በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርና አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2008

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 3

መግቢያ 3

የኤጀንሲው ራዕይ 4

የኤጀንሲው ዓላማ 4

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር 5

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል 6

ድርጅታዊ መዋቅር 6

የሰው ኃይል አደረጃጀት 7

የፋይናንስ ምንጭ 7

የኤጀንሲውና የልማት ድርጅቶች አሰራር ስርዓት መግለጫ (System Description) 8

የኮርፖሬት አመራር ዳይሬክቶሬት የሥራ ሂደት የአሰራር ስርዓት መግለጫ 8

የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ የአሰራር ስርዓት መግለጫ 8

የኦዲቱ ዓላማ 8

የኦዲቱ ዘዴና ወሰን 9

የኦዲቱ ወሰን 9

የኦዲቱ ዘዴ 9

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ 9

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች 9

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት 10

ክፍል ሁለት 12

የኦዲቱ ግኝቶች 12

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ 12

የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተመለከተ፣ 12

ቋሚ ንብረቶች በወቅቱ ምዝገባቸው የማይከናወን መሆናቸውና በተሟላ መልኩ የማይመዘገቡ መሆኑ፣ 14

በአዲስ መልክ ድርጅቶች ሲቋቋሙ ትክክለኛውን የሂሳብ ዋጋ የማይዙ መሆናቸው፣ 19

የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ ወቅታዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣ 20

የንብረት ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ መያዙን በተመለከተ፣ 23

ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን በተመለከተ፣ 25

ለንብረት ስራ የሚመደቡ ሠራተኞችን በተመለከተ፣ 30

የተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣ 31

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣ 32

ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣ 32

ለቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና መገባቱን በተመለከተ፣ 35

ለንብረቶች መለያ ቁጥር መሰጠቱን በተመለከተ፣ 36

ንብረቶችን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከል ተስማሚ የንብረት መጋዘን መኖሩን፣ 38

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣ 40

የንብረት አወጋገድን በተመለከተ፣ 40

ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎችን በተመለከተ፣ 46

ክፍል ሦስት 49

መደምደሚያዎች 49

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ 49

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣ 51

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣ 52

ክፍል አራት 53

የማሻሻያ ሃሳቦች 53

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ 53

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣ 54

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣ 555

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 566

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. መንግስት በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን ሚናና ተሳትፎ በመለወጥና የግሉን ክፍል ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን አስፈላጊ በመሆኑ የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ስር እስካሉ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው በመቀጠል የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም እነዚህን አላማዎች ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን በማዋሃድ ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በመባል በአዋጅ ቁጥር 412/1996 ተቋቁሟል፡፡
2. አጀንሲው በሥሩ የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶችን በውጤት ለመምራት፣ የልማት ድርጅቶች የገበያና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግና በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥና በመሳሰሉት መንገዶች አቅማቸውን በመገንባት ዘመናዊ የኮርፖሬት አመራር ሥርዓት ፕሮግራሞችን በመተግበር ውጤታማነታቸው እንዲሻሻል ለማድረግ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ አማራጮች ድርጅቶቹን ወደ ግል ይዞታ የማዛወርና የገበያ ክፍተት ያለባቸው መስኮችን በመለየት ክፍተቶቹን ለመፊተሽ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን በማስጠናት በመንግስት ሲፈቀድ ወደ ሥራ እንዲገቡና የገበያ ክፍተቶች እንዲሞሉ በማድረግ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡
3. ኤጀንሲው ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣትና የተገልጋዮቹን ፍላጎት ለማርካት የአሰራር ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በ2002 በጀት ዓመትም በዘርፍ ደረጃ የተጠናውን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የመምራትና ፕራይቬታይዝ የማድረግ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጠናቆ በመተግበር ላይ ይገኛል፣ ቀድሞ የተዘጋጀውን የተቋሙን የ2003-2007 ስትራቴጂክያዊ ዕቅድ መሰረት ያደረገና የዕቅድ ማስፈፀሚያ የሆነውን የተቀናጀ ሚዛናዊ የአፈፃፀም ምዘና ሥርዓት (Balanced Score Card (BSC) በማዘጋጀት በ2005 በጀት ዓመት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም በተልዕኮው ከተካተቱት መካከል የልማት

ድርጅቶችን አፈፃፀም በማሳደግ ለእድገትና ትራንስፎርሜሽኑ እቅድ መሳካት ድርሻውን ለማበርከት የድርጅቶች የአቅም ግንባታና ኦፕሬሽን ግቦች በእቅዱ እንዲሰሩ ሰፊ ጥረቶች አድርጓል፡፡

4. በመሆኑም የልማት ድርጅቶች በእጃቸው ያለውን ሀብታቸውን መዝግበው በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም የመቆጣጠር እና በአግባቡ ስራ ላይ የማዋል፣ የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ንብረቶችን በመለየት፣ አገልግሎታቸው ሲያበቃ ወይም አገልግሎት ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ የማስወገድ ስራ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ ችግሮች የሚስተዋሉ በመሆኑ ለእነዚህ ችግሮች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

የኤጀንሲው ራዕይ

5. ብቁና ተወዳዳሪ የሆኑ የልማት ድርጅቶች እየተፈጠሩ ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ አሰራር ወደ ግል ተዛውረው ማየት፣

የኤጀንሲው ዓላማ

6. ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 412/1996

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር በወጣው አዋጅ መሰረት የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራም ግልፅና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲፈጸም ማድረግ፤
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አቅማቸውን በተሻለ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ማስቻልና የተሻሻሉ የማኔጅመንት ሥርዓቶችንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻልና የላቀ ውጤት እንዲያመጡ ማገዝ፤
- ✓ በተለያዩ ምክንያቶች የግል ባለሃብቶች ሊሳተፉባቸው ባልቻሉ ለኢኮኖሚው አጠቃላይ ልማት ማነቆ ሊሆኑ በሚችሉ ዘርፎች አዳዲስ የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ማድረግ፤
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን አመራር መቆጣጠር ፤ እና

- ✓ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማኅበራት የመንግስትን የባለቤትነት መብት የማስከበር፡፡

የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

7. ኤጀንሲው በአዋጅ ቁጥር 412/1996 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-
   - ✓ የፕራይቬታይዜሽንን ፕሮግራም ማስፈጸም፣
   - ✓ ወደ ግል የሚዛወሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችንና የአክስዮን ይዞታዎችን ዝርዝር ለሚኒስቴሩ አቅርቦ ማስወሰን፣
   - ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ለማዛወር የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ እንዲከናወኑ ማድረግ፣
   - ✓ በፕራይቬታይዜሽን የሚሳተፉ ባለሃብቶች የሚወዳደሩባቸውን መመዘኛዎች መወሰን፣ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች ተሳትፎም ሊበረታታ የሚችልበትን መንገድ መቀየስ፣
   - ✓ ፕራይቬታይዜሽኑን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣
   - ✓ የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙና አፈጻጸሙ በህዝብ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ፣
   - ✓ የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ክትትል በማድረግ በፕራይቬታይዜሽኑ የተሳተፉ ባለሃብቶች የገቧቸውን ግዴታዎች ማክበራቸውን ማረጋገጥ፣ ፕራይቬታይዜሽኑ ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት መገምገም፣
   - ✓ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ሃሶቦች ገምግሞ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አቅርቦ ማጸደቅ፣ ተግባራዊነታቸውንም መከታተል፣
   - ✓ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አቅም ለመገንባት የሚረዱ ጥናቶችን በማካሄድ አጠቃላይ መመሪያዎችን መስጠት፣
   - ✓ ለመንግሥት የልማት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድና ሰብሳቢና አባላትን መመደብ፣ ማንሳት፣ አበላቸውን መወሰን፣
   - ✓ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የውጭ ኦዲተሮች ምደባ ማጽደቅ፣

- ✓ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አጠቃላይ ግቦችና የኢንቨስትመንት እቅዶችን ማጽደቅ፣
- ✓ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አፈጻጸም መከታተልና መገምገም፣
- ✓ በውጭ ኦዲተሮች የተመረመሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የሂሳብ ሪፖርት ማጽደቅ፣
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሂሳብ ከመዝገብ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸሙን መከታተል፣
- ✓ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ማዋሀድ ወይም መከፋፈል ሲያስፈልግ ተገቢውን ጥናት አካሂዶ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣
- ✓ ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሥራ አመራር ቦርድና የማኔጅመንት አባላት ተፈጻሚ የሚሆን በውጤት ላይ የተመሠረተ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፣ በሥራ ላይ እንዲውልም ማድረግ፣
- ✓ በአክስዮን ማህበራት የባለአክሲዮኖች ጉባኤ መንግሥትን መወከል፣ በመንግሥት በኩል የሚቀርቡ የዲሬክተሮች ቦርድ እጩ አባላትን መሰየም፣
- ✓ በሕግ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኞችንና የማኔጅመንት አባላትን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለሚቆዩበት ሁኔታ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት

የንብረት ባለቤት መሆን ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ ናቸው፡፡

የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

8. የቀድሞ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በፕራይቬታይዜሽን ቦርድ የሚተዳደር ሆኖ ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የነበረ ሲሆን ኤጀንሲው አንድ ዋና ዳይሬክተር የነበረው ሲሆን ዋናው ዳይሬክተር በስሩ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለትም የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና የፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም ስድስት ዳይሬክቶሮቶች ማለትም የዕቅድና የመረጃ ሥራ አመራር፣ የአሠራር ማሻሻያና የሰው ሃብት፣ የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን፣ የህግ፣ የኦዲት፣ የፋይናንስና አቅርቦት እና የሴቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡

በኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥር የኮርፖሬት አመራር እና የኮርፖሬት አቅም ግንባታና ድጋፍ ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም የፕራይቬታይዜሽንና የፕሮጀክት ጥናት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ስር የፕሮጀክት ጥናትና ትግበራ እና የፕራይቬታይዜሽን ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡

የሰው ኃይል አደረጃጀት

9. በአጠቃላይ ኤጀንሲው 326 ቋሚ ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን በነሐሴ 2006 ዓ.ም 198 ቋሚ ሠራተኞች ሲኖሩ 128 ክፍት የስራ መደብ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የሥራ ዘርፎች መካከል የኦዲት አካባቢው የኦፕሬሽን ዳይሬክቶሬትን የስራ ዘርፍ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ የስራ ዘርፍ 82 ቋሚ ሠራተኞች እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን ሰኔ ወር 2006 ዓ.ም በተገኘው መረጃ መሰረት 33 ቋሚ ሠራተኞና 49 ክፍት የስራ መደብ ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

10. የኤጀንሲው የገቢ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደብ በጀት ብቻ ሲሆን የገቢና የወጪ መግለጫው በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ገቢና ወጪ	2004 ዓ.ም.	2005 ዓ.ም.	2006 ዓ.ም
1.	መደበኛ በጀት	15,202,804.80	18,476,460.51	26,006,100.00
2.	መደበኛ ወጪ	11,901.789.44	15,804,092.13	20,315,386.70
አጠቃቀም በመቶኛ		78.29%	85.54%	78.12%

የኤጀንሲውና የልማት ድርጅቶች አሰራር ስርዓት መግለጫ (SYSTEM DESCRIPTION)

የኮርፖሬት አመራር ዳይሬክቶሬት የሥራ ሂደት የአሰራር ስርዓት መግለጫ

11. የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የልማት ድርጅቶቹ ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ ተግባራዊነቱን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ የልማት ድርጅቶች የሚመሩባቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል በየጊዜው እንዲሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋል፣ የተዘጋጁትን ደንቦችና መመሪያዎች በማፅደቅ እንዲሰራጩ ያደርጋል እንዲሁም በልማት ድርጅቶች መካከል ቅንጅትና ትስስር እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ የአሰራር ስርዓት መግለጫ

12. የልማት ድርጅቶቹ ቋሚ ንብረቶች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ ሁሉንም መረጃዎች አሟልተው ይመዘግባሉ፣ በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ያካሂዳሉ፣ በድርጅቱ ውስጥ ንብረቶችን በባለቤትነት የመከታተል ሃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል ቋሚ ንብረቱን መረጃ በማጣራት የሚወገዱ ንብረቶችን ዝርዝር በመያዝና አግባብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር የማስወገድና ከመዝገብ የመሠረዝ ሥራ ያከናውናሉ፡፡

የኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ኣላማ የልማት ድርጅቶቹ በንብረትና አወጋገድ ዙሪያ ያጋጠማቸውን ችግሮች መለየትና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅቶቹ ላጋጠማቸው ችግሮች የሰጠው ድጋፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳብለማቅረብና ሚንስቴር መ/ቤቱ ያለበትን ተጠያቂነት ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴና ወሰን

የኦዲቱ ወሰን

14. ኦዲቱ የሚከናወነው በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ዋናው መ/ቤት እና በተመረጡ 29 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ከ2004-2007 በጀት ዓመት በተሰሩ ሥራዎች ላይ ሲሆን ሥራው የሚያተኩረው የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አያያዝና አወጋገድ ሆኖ በመንግስት እጅ ካሉት የልማት ድርጅቶች ውስጥ በናሙና በሚመረጡ በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች እና ጉዳዩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የሚያካትት ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

15. በኦዲቱ ወቅት ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው አዋጆች፣ የኤጀንሲው ስትራቴጂክ ዕቅድ (ከ2003-2007ዓ.ም.)፣ የኤጀንሲው መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት (BPR Document)፣ ከ2004 በጀት ዓመት-ሰኔ 2006 ዓ.ም ድረስ ያለው የኤጀንሲው የተጠቃለለ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት፣ ከ2004 በጀት ዓመት ሰኔ 2006 ዓ.ም የልማት ድርጅቶች ዕቅድ አፈጻጸም የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ኤጀንሲው ያዘጋጀው የልማት ድርጅቶች የንብረት አያያዝና አወጋገድ መመሪያ፤ አዋጅ እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው የተለያዩ ማስረጃዎች ተከልሰዋል፡፡ በተጨማሪም ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ በማየት ተከናውኗል፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች

17. ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና ስድስት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Sub Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርን ለማከናወን የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም ኢኮኖሚን ማዕከል ባደረገና ውጤታማ በሆነ መልኩ ንብረቶቹ መጠበቃቸውን መገምገም፣

   1.1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረቶችን በብቃት ለማስተዳደር የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘርጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣

   1.2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረት በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን መገምገም፣

2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አወጋገድን ለማቀላጠፍ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑንና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ንብረቶች አወጋገድ ስኬታማና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣

   2.1 የንብረት አወጋገድ መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣

   2.2 ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ንብረቶች አወጋገድ ስኬታማና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣

3. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን ለመምራት የሚያስችል መመሪያዎችን ማውጣቱንና ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ማድረጉ እንዲሁም ከልማት ድርጅቶቹ ጋር በቅንጅት የሚሰሩት ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀሙን መገምገም፣

   3.1. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን ለመምራት የሚያስችል መመሪያዎችን ማውጣቱንና ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ማድረጉን ማጣራት፣

   3.2. ከልማት ድርጅቶቹ ጋር በቅንጅት የሚሰሩት ሥራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀሙን ማጣራት የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

18. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና ስድስት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 33 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criterias) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ

መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ኤጀንሲው የተቋቋመበት አዋጅ፣ የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የተለያዩ መመሪያዎች፣ መልካም ተሞክሮዎች እና ቃለ-መጠይቆች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ቀርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን ዝርዝሩም በአባሪ አንድ ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲቱ ግኝቶች

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

የንብረት አስተዳደር መመሪያን በተመለከተ፣

19. የመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚመለከተው የበላይ አካል የጸደቀ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ሊኖራቸውና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጂ በእርሻ መሣሪያዎች እና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማህበር የራሳቸው ንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ የሌለ መሆኑ የሚጠቀሙትም የፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያን መሆኑ እንዲሁም በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረት አስተዳደር መመሪያ የተዘጋጀው የካቲት 1996 ዓ.ም መሆኑና ወቅታዊ ሳይደረግ ከአስር ዓመት በላይ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

21. ይህን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መመሪያው ከተዘጋጀ የቆየ እንደሆነና ወቅታዊ ቢደረግ ጥሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ድርጅት የንብረት አስተዳደር ሃላፊው ተጠይቀው በሰጡት መልስ አ/ማህበሩ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ ገልፀው ተቋሙ በአዲስ መልክ ከተደራጀ በቅርብ ስለሆነ መሆኑንና ወደፊት ለማዘጋጀት እቅድ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

22. በዚህም ምክንያት በናሙና ባየናቸው አብዛኞቹ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአሰራር ላይ ከንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ችግሮች እንደተከሰቱ፡ መረጃ በሰበሰብንበት ወቅትና ከባለሙያዎቹ ጋር በተደረገ ውይይትና ቃለ መጠየቅ ለመረዳት የቻልን ሲሆን ለመጥቀስ ያህል ለንብረቶች መለያ ቁጥር አለመስጠት፣ ቆጠራ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ አለማካሄድና ቋሚ ንብረቶች መረጃቸው በትክክልና በተሟላ ሁኔታ አለመመዝገብ፣ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ አመዘጋገብ የተሟላ አለመሆን፣ ንብረቶች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸው ሲሆን

ሙያው የሚጠይቀውን አሰራር ካለመረዳትና ስልጠና ካለማግኘት አንፃር እንደሆነ፣ በተጨማሪም ተደጋጋሚ የስራ ጫና በመኖሩ፣ በሰው ሃይል እጥረት ችግር እንደሆነና ከመመሪያዎች ክፍተት ምክንያት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ከእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አክስዮን ማህበር ሃላፊዎች ጋር በተደረገ የመውጪያ ስብሰባ ወቅት በተደረገው ውይይት ድርጅቱ የፌዴራል መንግስትን የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ እንደሚጠቀም ገልፀው ተቆጣጣሪው ድርጅት ወደፊት የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ሲሰጣቸው እንደሚጠቀሙበትና ለአሁን ግን የፌዴራሉ መመሪያ በቂ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

24. ድርጅቶቹ የንብረቶቹን መረጃ በትክክልና በተሟላ ሁኔታ አለመመዝገባቸው፣ መለያ ቁጥር ባለመስጠታቸው፣ ንብረቶች ለጉዳት በተጋለጠ ሁኔታ በመገኘታቸው ምክንያት የመንግስት ንብረት በቀላሉ በመቀየር ጥቅም ለማግኘት የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥር፣ በተገቢ ሁኔታ ንብረቶችን ለመቆጣጠር እንዳይቻል ሊያደርግና ገንዘብ ወጥቶባቸው የተገዙ ንብረቶች ለብልሽትና ለጉዳት በመዳረግ መንግስትን ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

25. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ሃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ድርጅቱ በISO 9001-2008 የጥራት ሥራ አመራር መሠረት ያዘጋጀውን የንብረት አስተዳደር ሂደት አስጠንቶ ተግባራዊ እንዳደረገና ዝርዝር መመሪያው ከISO 9001-2008 ጥናት ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲዘጋጅ እንደሚደረግና ነባሩ መመሪያ ሣይሻሻል ለረጅም ዓመታት ሥራ ላይ መዋሉ ተገቢ እንዳልሆነ እንደተቀበሉት ገልፀዋል፡፡

26. በእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ እና በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ከመውጫ ስበሰባ በኋላ በተደረገው ማጣራት ተቆጣጣሪው ድርጅት በመጋቢት 2002 ዓ.ም ለልማት ድርጅቶቹ አዘጋጅቶ በሚያዛ 20, 2002 ዓ.ም ያሰራጨው የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያን ሊያቀርቡ ያልቻሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

27. እንዲሁም ተቆጣጣሪ መ/ቤቱ መንግስት ሙሉ ለሙሉ ባለቤት ለሆነባቸው የልማት ድርጅቶች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ የካቲት 2006 ዓ.ም ረቂቅ ቢያዘጋጅም አፅድቆ ለልማት ድርጅቶች ያላሰራጨ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

28. የተቆጣጣሪው መ/ቤት ሃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት እንደገለፁት የፋይናንስ መመሪያ ለልማት ድርጅቶቹ በሚያዛ 20, 2002 ዓ.ም አዘጋጅተው እንዳሰራጩና ሆኖም የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያው ከተዘጋጀ በጣም የቆየ በመሆኑ አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ወቅታዊ አድርገው ወደፊት ለመንግስት የልማት ድርጅቶቹ እንደሚያሰራጩ ገልፀዋል፡፡

29. መረጃ ከተሰበሰበባቸው የልማት ድርጅቶች ለማየት እንደተቻለው አብዛኞቹ የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ አዘጋጅተውና በሥራ አመራር ቦርድ አስፀድቀው ተግባራዊ እያደረጉ ቢሆንም አንዳንድ ድርጅቶች የንብረት አስተዳደር መመሪያ የሌላቸው መሆኑና መመሪያው ቢኖርም መሠረታዊ ጉድለቶች ያሉት በመሆኑ ምክንያት በልማት ድርጅቶቹ ከንብረት አስተዳደርና አወጋገድ ጋር በተያያዘ የአፈፃፀም ችግሮች መኖራቸውን ለማየት ችለናል እንዲሁም ተቆጣጣሪው መ/ቤት የመንግስት በልማት ድርጅቶቹ በርካታ የአፈፃፀም ችግሮች መኖራቸውን እያወቀ ለሁሉም የልማት ድርጅቶች የሚያገለግል ወቅታዊ፣ ወጥና አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሊያሰራ የሚችል የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ አውጥቶ አለማሰራጨቱ የልማት ድርጅቶቹ ያሉባቸውን ስህተት በተፈለገው ፍጥነት ሊያርሙ እንዲችሉ ያለማድረጉና የመንግስት ንብረት ላልተገባ ጥቅም ሊውል፣ ለብልሽትና ለጉዳት ሊዳረግ ይችላል፡፡

ቋሚ ንብረቶች በወቅቱ ምዝገባቸው የማይከናወን መሆናቸውና በተሟላ መልኩ የማይመዘገቡ መሆኑ፣

30. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በስራቸው የሚገኙ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ እቃዎች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት በመለየት መረጃቸውን በአግባቡ ሊይዙ ይገባል፡፡

31. ሆኖም በግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት በንብረት አስተዳደር ክፍል የቋሚ ንብረቶች ምዝገባ እንደሚከናወን በተደረገው ማጣራት ምዝገባውን በኮምፒውተር ለማከናወን ጅማሪ ሥራ ቢኖርም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣

ለምሳሌ ያህል፡-

- ✓ ከበላይ አብ ሞተርስ ፒኤልሲ በቀን 23/12/06 በቁጥር 2 ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 2,442,600 የሆኑ ሁለት ፒክ አፕ ተሸከርካሪዎች፣

- ✓ በቀን 28/12/06 ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 3,045,000 በቁጥር 3 የሆኑ ማሙት ኤኤምሲኢ. ተሽከርካሪዎች፣
- ✓ ኢቪኮ ትራክር በቀን 5/7/07 ከአምቼ የተገዛ በቁጥር 3 ጠቅላላ ዋጋቸው 9,061,086.24፣
- ✓ ቶሺባ ላፕቶፕ በቀን 6/8/07 ዋጋው ብር 23,000 የሆነ ምዝገባቸው ያልተከናወነ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. ጉዳዩን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ምዝግባውን ለማከናወን የጀመሩ ቢሆንም በክፍሉ ውስጥ ምዝገባ የሚያከናውኑት እሳቸው ብቻ እንደሆኑና የሰው ሃይል እጥረት ስላለ ሥራው ሊያልቅ እንዳልቻለና በዚህም ምክንያት ሰራተኞች በሚለቁበት ወቅት ምዝገባው በአግባቡ ስላልተከናወነ ንብረት የሌለባቸውን አለባችሁ እየተባለ መሆኑና ከጊዜም አንፃር ጫና እየተፈጠረባቸው እንዳለና በስራቸው ላይም ችግሮች እየተፈጠሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

33. በመውጪያ ስብሰባ ላይ ከድርጅቱ ግዢ፣ ንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ውይይት በአንዴ ሙሉ ለሙሉ ምዝገባውን ለማከናወን ንብረቶቹ በፊት ሳይመዘገቡ ለበርካታ ዓመታት የቆዩ በመሆኑ፣ አንዳንድ ቋሚ ዕቃዎችን ለመመዝገብ ሰነዶቹ ከ20 ዓመታት በላይ የቆዩ መሆናቸው መረጃዎችን ለማስፈር በማስቸገሩና ሥራውን ለማከናወን ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ በተሟላ ሁኔታ ምዝገባው እንዳልተከናወነ ወደ ፊት ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀዋል፡፡

34. በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች በቋሚ እቃዎች መዝገብ ላይ በወቅቱ የማይመዘገቡ መሆኑን፣

ለምሣሌ ያህል፡-

- ✓ ለድርጅቱ እንጨትና ብረታ ብረት ማምረቻ የሚያገለግል በብር 2,681,191.39 የተገዙት metal cutting and Glass polishing machine በቋሚ እቃነት ተመዝግበው ያልተገኙ መሆኑን፣
- ✓ በ2006 ዓ.ም ከተገዙ ቋሚ እቃዎች ውስጥ እስከ 24/4/07 ድረስ በቋሚ እቃዎች ስር ተካተው ያልተመዘገቡ/ያልተያዙ/ የነበረ መሆኑ፣

- ✓ ለድርጅቱ አገልግሎት የሚውሉ ከጄኔራል ኤክስፖርት በኤልሲ ቁጥር 846 የተገዙት የተለያዩ ኬሚካሎች፣ የባይሎጂ፣ የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪ አፓራተስ እና የሳይንስ ኪትስ ጥሬ እቃዎች በቀን 7/11/06 የኢንስፔክሽን ስራው እና በቀን 15/11/06 ዓ/ም የዋጋው ግንባታው ተጠናቆ ለሚመለከተው የስራ ክፍል የተላከ ቢሆንም እስከካሁን ድረስ የገቢ ሰነድ ያልተቆረጠላቸውና ምዝገባቸውም ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ የህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ካሉበት ጊዜ ጀምሮ የአመዘጋገብና አያያዝ ችግር የነበረበትና ያልታረቀ በመሆኑ ከፍተኛ ጉድለትና ብልጫ ያስከተለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. ጉዳዩን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የጄኔራል አፓራተስ ከውጭ ተገዝተው የመጡ ንብረቶች እንደሆኑና የመለየት ችግር ስላጋጠማቸው ወደ ስድስት ወር እንቆዩ፣ ርክክብና የመለየት ሥራው ጊዜ የፈጀ መሆኑና በተለይ የመለየት ሥራው በጥንቃቄ መታየት ስለነበረበትና እንዲሁም ሲለዩ ኤክስፓይር ዴት ያልተፃፈባቸው ስለነበሩና ወደ ግገርው አካል መመለስ ስለነበረበት ከነሱ የሚስፈልጉትን እንደ ሪቴንሽን ያሉ ነገሮች ቢያልቁም ሊዘገዩ እንደቻሉ በአሁን ወቅት ግን የገቢ ሰነድ ተቆርጦ ምዝገባው እንደተካሄደ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

36. መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ከተለያዩ ሰነዶች ለማየት እንደቻልነው በ2006 በጀት ዓመት ከተገዙት ዕቃዎች ውስጥ የገቢ ሰነድ ተቆርጦላቸው ገቢ ቢደረጉም ለአቅራቢዎቹ ድርጅቶች የተከፈለ የመጨረሻ ክፍያ ሰነድ የባንክ ክፍያ አድቫይስ ባለመመዘገቡ በጉዞ ሂሳብ ላይ ያለውን የሂሣብ ቋት ንብረት ሊመዘገብ እንዳልቻለና ከህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ጋር በተያያዘም የንብረቶች አለመመዝገብና አለመታረቅ በውስጥ ኦዲተሮች በተደጋጋሚ ጊዜ አስተያየት ቢሰጥም ችግሩ አሳሳቢ በመሆኑ ካልተስተካከለ ግዜ ከወሰደ በኋላ ለማስተካከል እንደሚያስቸግር ተገልጿል፡፡

37. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች በኮምፒውተር የቋሚ እቃዎች መዝገብ ላይ በወቅቱ የማይመዘገቡ መሆኑን፣ ለመጥቀስ ያህል ፡-

- ✓ ዴል ኮምፒውተር በ11/01/08 በብር 11,600 የተገዛ ምዝገባው ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ ባይንዲንግ ማሽን በብር 2,000 በቀን 21/11/07 የተገዛ ምዝገባው ያልተከናወነ መሆኑ መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

38. ይህም የሆነበት ምክንያት ቆጠራ የተካሄደበት ወቅት ስለነበረና አሁን ደግሞ የውጭ ኦዲተሮች ሥራ ሊጀምሩ ስለሆነ ተደራራቢ የሆነ ሥራ በማጋጠሙ እንደሆነ ከእርሻ መሳሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የስቶክና ምዝገባ ኦፊሰርከኦዲት ቡድኑ ጋር ባደረጉት ውይይት ወቅት ገልፀዋል፡፡

39. ጉዳዩን አስመልክቶ ከድርጅቱ ሃላፊዎች ጋር በመውጪያ ስብሰባ ወቅት በተደረገ ውይይት ንብረቶች በካርድም በኮምፒውተር ምዝገባቸው እንደሚከናወን እንደሚያውቁና በድርጅቱ ግን ምዝገባ የሚያከናወነው በካርድ መሆኑና በኮምፒውተር ለመያዝ ከINSA (Information Network Security Agency) ጋር ከአንድ ዓመት በፊት ሥራውን ለማሰራት ስምምነት እንደተፈራረሙና ድርጅቱ እየሰፋ ስለሄደ ወደፊት ቀልጣፋ አሰራር ከማስፈን አንጻር ድርጅቱ የተጠናከረ አካሄድ ለመተግበር ዕቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

40. በኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር ቋሚ እቃዎች ከተገዙ በኃላ ከአንድ አመት በላይ ሳይመዘገቡ እና የእርጅና ተቀናናሽ ያልተሰላቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ የቋሚ ዕቃዎች ገቢ ማድረጊያ ሰነዶች ሲዘጋጅ የዕቃው መለያ ኮድ ተሟልቶ የማይመዘገብ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም መመሪያው በሚጠይቀው መሰረት ምዝገባው የማይከናወን መሆኑ ለመጥቀስ ያህል በግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት የንብረት አስተዳደር መመሪያው ቋሚ ንብረቱ የተገዛበት ቦታ እና የዋስትና ጊዜ ማካተት አለበት ቢልም በምዝገባው ውስጥ እነዚህ መረጃዎች ያልተካተቱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

41. ይህን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ እስካሁን ያሉትን ስራዎች የተሰሩት በራሳቸው ጥረት እንደሆነና መመሪያው ላይ የተቀመጠ ፎርማት የሌለ መሆኑ ወደ ፊት ድርጅቱ አዘጋጅቶ የሚሰጣቸው ከሆነ ለመሥራት ዝግጁ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

42.የግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት ሃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ምዝገባው የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ለማሟላት ስራው የተጀመረ ሲሆን ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ በተጨማሪም በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ metal cutting and Glass polishing machine በተመለከተ እቃው ከውጭ መጥቶ ክፍያዎች በሙሉ ያልተጠናቀቁ ስለነበሩ ያልተመዘገቡ እንደነበረና Cost-build up እንደተጠናቀቀ በዚያው በጀት ዓመት በቋሚ ንብረት ላይ እንደተመዘገበ፣ ኬሚካሎች በርካታ ዓይነት የነበሩ በመሆኑ በዝርዝር ዋጋ እስኪወጣላቸው ድረስ ያልተጠበቀ ጊዜ እንደፈጀና ሆኖም የበጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ምዝገባው ተጠናቆ በስቶክ እንደተያዘ የህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤትን በተመለከተ በድርጅቱ የውስጥ ኦዲት ምርመራ ተደርጎ በታየው ጉድለትና ብልጫ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተወሰደና በአሁኑ ወቅት ምዝገባው እንዲታረቅ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

43.እንዲሁም የኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለተዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ከአስተያየቱ በኋላ ቋሚ ንብረቱ ተመዝግቦ የእርጅና ስሌት እየተሰራለት ከመሆኑም ሌላ የቋሚ ንብረት መዝገብ ተዘጋጅቶ ተገዝተው የሚገቡ ቋሚ ንብረቶች እየተመዘገቡ እንደሚዘጋጁ ገልፀዋል በተጨማሪም የግብርና ምረት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት ሃላፊዎች በሰጡት መልስ የቋሚ ንብረቶችን ምዝገባው የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ለማሟላት ስራው የተጀመረ መሆኑ፣ ወደፊትም ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

44.በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ ከመውጪያ ስብሰባ በኋላ በተደረገው ማጣራት በናሙና ካየናቸው ውስጥ ዴል ኮምፒውተር በ11/01/08 በብር 11,600 እና ባይንዲንግ ማሽን በብር 2,000 በቀን 21/11/07 የተገዛ ምዝገባቸው በድርጅቱ የፊክስድ አሴት ሬጅስትሬጅሽን ካርድ ላይ እና በኮምፒውተር ላይም ምዝገባው መደረጉን ብናይም ነገር ግን ሁሉም የተገዙ ቋሚ ዕቃዎች በወቅቱ ምዝገባቸው ይካሄዳል ብሎ ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡

45.እነዚህ አይነት አሰራሮች የልማት ድርጅቶቹ የንብረቶቹን ሁኔታ አውቀው በአግባቡ ክትትልና ቁጥጥር እንዳያደርጉ ካለማስቻሉም በላይ ድርጅቶቹን ለአሰራር ክፍተት በመፍጠር የመንግስት ንብረት ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

በአዲስ መልክ ድርጅቶች ሲቋቋሙ ትክክለኛውን የሂሳብ ዋጋ የማይዙ መሆናቸው፣

46. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ የነበራቸውን ንብረት ትክክለኛው ዋጋ በመነሻ ሂሳብ ሊይዙ ይገባል፡፡

47. በኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር የመነሻ ካፒታሉ የተከፈለ ተብሎ በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ብር 68,899,000 እያለ በመዝገብ የተመዘገበው ግን ብር 54,059,520 ብቻ መሆኑ፣ በእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ እንደ አዲስ በአክሲዮን ማህበር ሲቋቋም የነበረው የንብረት ዋጋ ብር 174,000,000 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 94,000,000 የሚገመት ንብረት አክሲዮን ማህበሩ መርጦ እንዲወስድ ከተደረገ በኋላ የተቀረው ለባለአደራ ቦረድ እዲያስረክብ ከታዘዘ በኋላ ባለአደራ ቦርድ ግን ንብረቱን የማስቀምጥበት መጋዘን የለኝም በሚል ምክንያት እስካሁን ለ13 ዓመታት የንብረቱ ዓይነት ምን እንደሆነና በመዝገብ ላይ ሳይመዘገብ መቆየቱና ንብረቶቹ ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

48. ጉዳዩን አስመልክቶ ከእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ ሃላፊዎች ጋር በመውጫ ስብሰባ ወቅት በተደረገ ውይይት ሁሉም ንብረቶች የአ/ማህበሩ ንብረቶች የነበሩ ሲሆን ነገር ግን በንብረት ክፍፍል ወቅት አ/ማህበሩ የራሱ የሆኑትን ንብረቶች ለይቶ ምዝገባውን ያከናወነ መሆኑና ነገር ግን የባለ አደራ ቦርድ ንብረቶች ድርጅቱ ንብረቶቹን የማላቅ ስለሆነ፣ ንብረቶቹን ለይቶ ለመወሰድም ባለሙያ የለኝም በተጨማሪም ንብረቶቹን የማስቀምጥበትም ቦታ የለኝም በሚል ምክንያት ንብረቶቹን ማንሳትና መውሰድ ያልቻለ ቢሆንም ነገር ግን እነሱ ንብረቶቻቸውን በሃላፊነት ተረክበው ምዝገባውን ያከናወኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. ሆኖም ለንብረቶቹ ምዝገባ እንዳከናወኑ የሚገልፅ ማስረጃ ሊያቀርቡ አለመቻላቸውና መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት በርካታ የባለ አደራ ቦርድ ንብረቶች የሆኑ ተሸከርካሪዎችና ሌሎች ንብረቶች አሁንም በአ/ማህበሩ ግቢና ከድርጅቱ ውጪ በሆነ መጋዘን ውስጥ እንደሚገኙና በተለይ ተሽርካሪዎቹ ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ ከ13 ዓመት በላይ በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል፡፡

50. የኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለተዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ድርጅቱ በ1999 ዓ.ም አክስዮን ማህበር ሆኖ እንደገና ሲቋቋም በMemorandium of association ላይ authorized capital እና paid up capital ተብሎ የተመዘገበው ብር 68899000 ከ 1998 ዓ.ም የአክስዮን ማህበሩ በኦዲት

የተረጋገጠ ሂሳብ ላይ የተወሰደ ሲሆን፣ ብር 54,059,520 ከድርጅቱ ግንባታ ስራ መጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የተለቀቀ ገንዘብ መጠን በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ ከኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ጥያቄው ቀርቦ በክትትል ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

51. በፍል ውሀ አገልግሎት ድርጅት በሸበሌ ሆቴሎች አስተዳደር ሥር የነበረው የላንጋኖ ሎጅ ለፍል ውሃዎች አስተዳደር ሲተላለፍ የቋሚና አላቂ እቃዎች መነሻ ሂሳብ ሳይታወቅ የተላለፈ መሆኑና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ የመነሻ ሂሳቡ የማይታወቅና በፍል ውሃዎች አስተዳደር የንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ ቀደም ሲል በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ሥር ሲተዳደር የነበረውን የላንጋኖ ሪዞርት ሆቴል በቁጥር መልድ 76-257/4103 በቀን ጥር 6/2003 ከፐ/መ/ል/ድ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በተፃፈ ደብዳቤ ከጥር 20/2003 ዓ.ም ጀምሮ ድርጅቱ ተረክቦ እያስተዳደረው እንደሚገኝና ነገር ግን በርክክቡ ወቅት ቋሚ ንብረቶችን /Physical Count/ በማድረግ ርክክብ የተካሄደ ሲሆን፣ ሂሳቡን ዘግቶ በወቅቱ ለማስመርመር ያልተቻለ መሆኑና በአሁኑ ወቅት ግን ከፐ/መ/ል/ድ ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በቁጥር መልድ 76-219/5/06 መስከረም 9/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በተሰጠው መመሪያ መሰረት የሃብት ትመና /Asset Valuation/ ተደርጎ የመነሻ ሂሳቡ ተሰርቶ የላንጋኖ ሂሳብ ከጥር 20/2003 ጀምሮ እስከ 2006 በጀት ዓመት በውጭ ኦዲተር እንደተመረመረ ገልፀዋል፡፡

53. ይህ አይነት አሰራሮች እነዚህን የልማት ድርጅቶች የንብረቶቹን ሁኔታ አውቀው በአግባቡ ክትትልና ቁጥጥር እንዳያደርጉ ካለማስቻሉም በላይ ድርጅቶቹን ለአሰራር ክፍተት በመፍጠር የመንግስት ንብረት ለአደጋ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ ወቅታዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣

54. የንብረት አስተዳደር የሚያከናውነው የሥራ ክፍል የተጠናቀረ መረጃ የያዘ የቋሚ ንብረት መመዘግቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም መዝገቦች ወቅታዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች ውስጥ፡-

በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፡-

- ✓ ከሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በኃላ በአብዛኛዎቹ ዕቃ ግምጃ ቤቶች ገቢና ወጪ የተደረጉ ንብረቶች በዕቃ ግምጃ ቤት በሰቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡና ከፋይናንስ እስቶክ ካርድ ጋር የማናበብና የማስታረቅ ስራ አለመሰራቱ፣
- ✓ የድርጅቱ ቋሚ እቃዎች በቋሚ እቃዎች ንብረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ በ2007 በጀት ዓመት ሁለተኛው ሩብ ዓመት ላይ ኦዲት ሲደርግ ለድርጅቱ እንጨትና ብረታ ብረት ማምረቻ የሚያገለግል በብር 2,681,191.39 የተገዙት metal cutting and Glass polishing machine በቋሚ እቃነት ተመዝግበው ያልተገኙ መሆኑን ለማወቅ መቻሉ፣
- ✓ በ2006 ዓ.ም ከተገዙ ቋሚ እቃዎች ውስጥ እስከ 24/04/07 ድረስ በቋሚ እቃዎች ስር ተካተው ያልተመዘገቡ/ያልተያዙ/መሆኑ፣
- ✓ ንብረቶች ዕቃ ግምጃ ቤት ሲገቡም ሆነ ሲወጡ የንብረት ገቢና ወጪ ሰነዶች ተቆርጦላቸዉ በእያንዳንዱ ዕቃ ግምጃ ቤት ቢን ካርዱና እስቶክ ካርድ ላይ በወቅቱ እየተመዘገበ መቀናነስ ያለበት ሲሆን የድርጅቱን ንብረት ለመቆጣጠር በተቋቋመው የንብረት ምዝገባና ኮስት ትንተና ቡድንም በፋይናንሻል ስቶክ ካርድ ላይ በየቀኑ እየተመዘገበ ከእቃ ግምጃ ቤት ምዝገባ ጋር በየወሩ እየተናበበና እየታረቀ ሪፖርት ሊቀርብ ሲገባ በወቅቱ እንደማይመዘገብና እንደማይታረቅ

  ለመጥቀስ ያህል፡-

  - ✓ የRound Pipe ባላንስ ላይ ከፍተኛ ልዩነት መታየቱ የገቢና የወጪ ሰነድ ሳይዘጋጅለት ስራ ላይ መዋሉ እና የመበየጃ መስታወትም ከሀምሌ ወር 2005 ጀምሮ በስቶክ ካርድ አለመመዝገቡና አለመቀናነሱ፣
  - ✓ የህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረቶች ካሉበት ጊዜ ጀምሮ የአመዘጋገብና አያያዝ ችግር የነበረበትና ያልታረቀ በመሆኑ ከፍተኛ ጉድለትና ብልጫ ማስከተሉ፣
  - ✓ ከውጭ ሀገር ተገዝተው ገቢ የሆኑ ንብረቶች መከታተያ መዝገብ በፋይናንስ እና ግዥ ዳይሬክቶሬት ውስጥ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

56. መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ከተለያዩ ሰነዶች ለማየት እንደቻልነው የመጋዘን ሃላፊዎች በስራ ጫና ምክንያት ምዝገባውንና የማስታረቁን ስራ ሊያከናውኑ እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

57.በግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት፡-

- ✓ ከግንቦት 4, 2006 ዓ.ም በኋላ ለተገዙት ቋሚ ዕቃዎች በንብረት መከታተያ መዝገብ ላይ ምዝገባቸው ያለመከናወኑ እንዲሁም በዕቃ ግምጃ ቤት በሰቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡና ከፋይናንስ እስቶክ ካርድ ጋር የማናበብና የማስታረቅ ስራ አለመሰራቱ፣
- ✓ የቢን ካርድ እና የስቶክ ካርድ አመዘጋገብ የተሟላ ያለመሆኑ፣
- ✓ በድርጅቱ የተለያዩ የእቃ ግምጃ ቤቶች በተደረገው ምልከታ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ አብዛኛው ቁጥሮቹ የሚበላለጡ መሆኑ፣
- ✓ በአሮጌ እቃ ማስቀመጫ መጋዝን ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- ✓ ለአዳዲስ እቃዎችም አልፎ አልፎ ስቶክ ካርድ የማይዘጋጅ መሆኑ በምልከታ ወቅት ለማየት መቻሉ፣
- ✓ በትራንስፖርት ሥር በሚገነኘው መጋዘን ሥር አንዳንድ ንብረቶች ቢን ካርድ የማይዘጋጅላቸውና ቢን ታግም ያልተለጠፈባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

58. ይህን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ምዝገባውን በራሳቸው ጥረት እየመዘገቡና ለማስታረቅ ጥረት እያደረጉ መሆኑና ነገር ግን በሰው ሃይል እጥረት ምክንያት ሥራዎች በሚፈለገው መልኩ እየተካሄዱ እንዳይደለ በዚህም ምክንያት በሰራቸው ላይ ጫና እየፈጠረ እንዳለና ሥራዎችን በአግባቡ ለመስራት እንደተቸገሩ ገልጸዋል፡፡

59. በተጨማሪም ሌሎች ተደራራቢ ስራዎች በመኖራቸው፣ ለስራውም አዲስ ስለሆኑ፣ ርክክቡም እስካሁን ስላልተጠናቀቀ እና በሰው ሃይል እጥረት ምክንያት መሆኑን ጉዳዩን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

60.በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ

- ✓ ከሀምሌ 2007 ዓ.ም ለተገዙት ቋሚ ዕቃዎች በኮምፒውተር ንብረት መከታተያ መዝገብ ላይ ምዝገባቸው ያለመከናወኑለመጥቀስ ያህል ዴል ኮምፒውተር በቀን 11/1/08 በብር 11600 የተገዛ፣ ባይንዲንግ ማሽን በ21/11/07 በብር 2000 የተገዛ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጊዜ ድረስ

በኮምፒውተር የቋሚ ዕቃ መመዝገቢያ ላይ ምዝገባቸው ያልተከናወነ መሆኑ ለማወቅ ችለናል፡፡

61. ይህም የሆነበት ምክንያት ቆጠራ የተካሄደበት ወቅት ስለነበረና አሁን ደግሞ የውጭ ኦዲተሮች ሥራ ሊጀምሩ ስለሆነ ተደራራቢ የሆነ ሥራ በማጋጠሙ እንደሆነ ከእርሻ መሳሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የስቶክና ምዝገባ ኦፊሰር ከኦዲት ቡድኑ ጋር ባደረጉት ውይይት ወቅት ገልፀዋል፡፡

62. የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለተዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ ግምጃ ቤቶች በስቶክ ካርድ በመሙላት በኩል አልፎ አልፎ መዘግየት ከመታየቱ በስተቀር በተለይ በበጀት መዝጊ ላይ ምዝገባ ሣይጠናቀቅና ከፋይናንስ ካርድ ሣይታረቅ ሂሣብ ተዘግቶ እንደማያቅ ወደ ፊትም መዘግየት እንዳይኖር ጥብቅ ክትትል እንደሚደረግ ሜታል ከቲንግና ግላስ ፖሊሺንግ ማሽንን በተመለከተ ምዝገባው መዘግየቱ አግባብ እንዳልሆነና በ 2007 በጀት ዓመት ንብረት ቆጠራ ወቅት እንዲመዘገብ ተደርጎ ማስተካከያ እርምጃ እንደተወሰደ፣ ድርጅቱ በርካታ መጋዘኖች ያሉት እንደሆነና አንዳንድ መጋዘኖች ላይ የተወሰነ የምዝገባ መዘግየቶች እንደታዩ ድክመት የታየበት መጋዘንም በመለየቱ የማስተካከያ እርምጃ በመወሰድ ላይ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

63. በመሆኑም የልማት ድርጅቶቹ የቋሚ ንብረት መመዝግቢያ ካርድና መዝገብ በትክክል ካልያዙ፣ መዝገቦች ወቅታዊ መደረጋቸውን ካልተከታተሉ እንዲሁም ቢን ካርድና እስቶክ ካርድ በትክክል እየተመዘገቡ የማናበቡና የማስታረቁ ስራ ካልተከናወነ ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ በትክክል አውቆ በአግባቡ እንዳይከታተሉ ካለማስቻሉም በላይ ንብረቶቹን ለመቆጣጠር እንዳይቻል በማድረግ ለአሰራር ብልሹነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

የንብረት ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ መያዙን በተመለከተ፣

64. የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውነው የሥራ ክፍል የንብረቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ ሊይዙ ይገባል፡፡

65. ሆኖም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ቋሚ ንብረቶቹ በየትኛው ሰራተኛ እጅ የሚገኙ ስለመሆኑ በኮምፒውተር ምዝገባውን ለማከናወን የተጀመረ

ሥራ ቢኖርም ምዝገባው ያለመጠናቀቁ እንዲሁም ምዝገባው የተከናወነውም በአብዛኛው የሚጠይቀው መረጃዎች ማለትም ዕቃው የሚገኝበት ቦታ፣ የተረከቡት ሠራተኛ ሥም፣ ብዛት የማይገለፅ መሆኑ መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ለማወቅ ታውቋል፡፡

66. በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የድርጅቱ ቋሚ ንብረቶች የት እና በማን እጅ እንዳሉ ለመለየት ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሰራ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ አለመጠናቀቁ፣ በአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ ሰራተኞች ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ቋሚ ዕቃዎች ሳያስረክቡ መ/ቤቱን ሲለቁ የሰራተኞች አድራሻ ሲጠፋ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ እንዲደረጉ ውሳኔ የማይሰጥ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

67. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ አንዳንድ ሠራተኞች ንብረት ፈርመው ከመጋዘን ሲወስዱ ከመጋዘን የወሰዱ ስለመሆኑ የሚገልፅ ሰነድ የንብረት ክፍል ሃላፊ ሰነዱን ለንብረት ክፍል ስለማይልክ ንብረቶቹ በማን እንደተወሰዱ ሊታወቅ ያለመቻሉ፣ እንዲሁም ቋሚ ንብረት መዝገቡ በማንዋል የተያዘ በመሆኑ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ተቀላቅሎ በመገኘት ሌሎችን ላልተረከቡት ንብረት በሃላፊነት እንዲጠየቁ እያደረገ መሆኑና ይሄን ችግር ለመፍታት በኮምፒውተር ምዝገባ ለማከናወን ጅምር ሥራ ቢኖርም ብዙም ሥራው አመርቂ ደረጃ ላይ የማይገኝ መሆኑ፣ በተጨማሪም የንብረት ተጠቃሚ ለሆኑ ሰዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

68. ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲት ወቅት በተደረገው ቃለመጠቅ፣ ውይይትና ካየናቸው ሰነዶች እነዚህ ስራዎች ያልተሰሩበት ምክንያት በቂ የሰው ሃይል ባለመኖሩ፣ በጊዜ እጥረት ምክንያትና አሰራሩን ካለመረዳት ስራዎችን ሊያከናውኑ እንዳልቻሉ ለመረዳት ችለናል፡፡

69. በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት መልስ በአሁኑ ወቅት ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር የመስጠት ሥራው እንደተጠናቀቀ ገልፀዋል፡፡ በአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ ድርጅት ግኝቱ በወቅቱ የነበረ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት ማስተካከያ እርምጃ ተወስዶ ንብረቶቹ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገው ለአገልግሎት የሚፈለገው መምሪያ ወይም አገለግሎት ከንብረት ክፍል ወጪ እያደረገ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

70.በዚህም ምክንያት ሰራተኞች ከድርጅቶቹ በሚለቁበት ጊዜ ምዝገባው በትክክል ስላልተካሄደ ንብረት የሌለባቸውን አለባችሁ እተየባሉ እዳ ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርግና ከጊዜ አንፃር በስራቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡

ዓመታዊ የንብረት ቆጠራን በተመለከተ፣

71. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሊያካሂዱና የቆጠራ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በቆጠራው የተገኘውም ከምዝገባው ጋር ማመዛዘን ይኖርባቸዋል፡፡

72. ይሁን እንጂ የእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ በ2006 በጀት ኣመትበቆጠራ ስራ ላይ የሚመደቡ ሰራተኞች በዓመት ዕረፍት ላይ እያሉ የተመደቡ በመኖራቸው ቆጠራው በወጣለት የጊዜ ገደብ ፀሐፊዎችን አሟልቶ ማስጀመር አለመቻሉ፣ ንብረታቸው የአደራ ቦርድ የሆኑ ንብረቶችን ለረጅም ጊዜ እንቅስቃሴ ሳይኖራቸው በየዓመቱ ቆጠራ የሚከናወን መሆኑ፣ በቁጥር 2 ዕቃ ግ/ቤት ከፍተኛ መጠንና ዋጋ የያዘ የባለአደራ ቦርድ ንብረት እንቅስቃሴው አዝጋሚ የሆነና በየዓመቱ እንቅስቃሴ የሌለው ንብረት ለመቁጠር መጋዘኑ ለሠራተኞቹ ደህንነት አመቺ አለመሆኑ ሠራተኞች በዚህ ግ/ቤት ተመድበው መስራት ፈቃደኛ አለመሆናቸው የሚመደቡትም ሠራተኞች በጤና ችግር ላይ መውደቃቸው ታውቋል፡፡

73. በተጨማሪም በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የክሌም ዕቃዎች በኮንቴነር ውስጥ በአንድ ላይ ተይዘው የሚገኙ ሲሆን የራሳቸው መቆጣጠሪያ ካርድ የሌላቸውና ያለመደርደሪያ የተከማቹ መሆኑ፣ በየዓመቱ በሚደረግ ዓመታዊ ቆጠራ ማንኛውም በአ/ማህበሩ ሥር ያለ ንብረት መቆጠር ሲኖርበት የክሌም ዕቃዎች ቀደም ባሉ ዓመታት/በ2002 እና 2003/ የተቆጠሩ ሲሆን ቆጠራው ከምዝገባው ተመሳክሮ የልዩነት መግለጫ /ልዩነት ከነበረ/ ያልቀረበበት ሲሆን በ2004 በጀት ዓመት ደግሞ ጭራሹን ያልተቆጠረ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. እንዲሁም በዋናው መሥሪያ ቤት ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 211፣ 212፣ 220፣ 221፣ 223 እና 224 ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ለመቆጠር ቁልፋቸው በማን እጅ እንደሚገኝ ባለመታወቁ መቁጠር አለመቻሉ፣ በጥገናና መገጣጠም ኢንጂነሪንግ ወርክ ሾፕ ያሉት ዲያግኖሲስ ዩኒት ለኢንስፔክሽን የሚገለገሉበት ቋሚ ንብረት

የተረከቡት ሠራተኛ የማስረከበው ንብረት ስለሆነ በሚል ምክንያት ሊያስቆጥሩ ፍቃደኛ አለመሆናቸው፣ በፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ውስጥ በቢሮ ቁጥር 101 ያሉትን ኮምፒውተሮች ተቆጥረው ፈራሚ አለመኖሩ፣ የቢሮ መገልገያ ንብረቶች፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ሼልፎች፣ መደመሪያ ማሽኖች ከመዝገብና ከቆጠራው ጋር ሊታረቁ አለመቻሉ ምክንያቱም በ1994 ዓ.ም የድርጅቱ አጥኚ የሰጠው ቁጥር ስለማይገጥም የማስታረቅ ሥራው አስቸጋሪ መሆኑ፣ ቋሚ ንብረቶች በዓመታዊ ቆጠራ ወቅት ቢቆጠሩም የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ጋር የማስታረቅ ስራ እንደማይከናወን ተገልጿል፡፡

75. በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በ2004 በጀት ዓመት የበጀት ዓመቱ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ከመዝገቡ ጋር የታረቀበት ምርመራ ለውጭ ኦዲተሮች አለመቅረቡ፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመት የህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ካለፉት ጊዜያት ጀምሮ የአመዘጋገብና አያያዝ ችግር የነበረበት እና ያልታረቀ በመሆኑ ከፍተኛ ጉድለት እና ብልጫ ማስከተሉ፣ ከንብረት ምዝገባና ኮስት ትንተና ቡድን ምዝገባ ጋር አለመታረቁ፣ በቆጠራ ወቅት መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው ዕቃዎች መኖራቸው መታወቁ፣ ራውንድ ፓይፕ በዕቃ ግምጃ ቤት ስቶክ ካርድ የሚታይ ባላንስ ብዛት 25 ሲሆን ያለው ክምችት ግን ከፍተኛ በመሆኑ መቁጠር አለመቻሉ እና በገቢ ሰነድ ቁጥር 009601በ26/2/06 ገቢ የሆነው ብዛት 850 በስቶክ ካርድ አለመመዝገቡና ወጪ የሆኑትን አለመመዝገባቸው፣ የመበየጃ መስታወት መለያ ቁጥር 05-01-0065 በ20/12/05 የተመዘገበ ባላንስ 70 ሲሆን በ26/02/06 ዓ.ም ቆጠራ ሲደረግ የተገኘው ባላንስ 58 መሆኑና ከሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮም ስቶክ ካርድ አለመቀናነሱ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

76. እንዲሁም ቆጠራ ከሰኔ 30 በኋላ ለብዙ ወራት የሚቆይ መሆኑና የቆጠራው ውጤትም ለማኔጅመንት ዘግይቶ የሚቀርብ መሆኑ ለመጥቀስ የ2006 ዓ.ም የቆጠራ ውጤት እስከ የካቲት 2007 ዓ.ም ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣ በቆጠራ ወቅት በሚመለከታቸው አካላት (የመጋዘን ሃላፊና ቆጠራውን በሚያከናውኑት ሠራተኞች) መካከል መተማመኛ የማይፈረም መሆኑ እና ቆጠራው በትክክል ስለመከናወኑ የሚያረጋግጠውም ሠራተኛ የማይፈርም መሆኑ፣ ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሲደረግ ቆጠራውን ያካሄዱት ሰራተኞች አለመገለፃቸውና መተማመኛም አለመፈረሙ፣

በእንጨትና ብረታብረት መጋዝን ውስጥ በርካታ ብረቶች በአይነታቸው ሳይለዩና ለቆጠራ በማያመች መልኩ በአንድ ላይ ሆነው ወለሉ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

77. ይህን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የፋይናንስ ስራ አስፈፃሚ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የ2007 ዓ.ም ችግር የሌለ መሆኑ ቆጠራው ሃምሌ 3 2007 ዓ.ም እንደተጠናቀቀ የሚመለከታቸው አካላት ተፈረርመው ያዘጋጁት ሰነድ መኖሩንና የማስታረቁ ስራ የተወሰኑ የተጀመሩ ስራዎች መኖራቸውና የሚመለከታቸው አካላቶች ገና የመፈረምና የመተማመን ስራ እንዳልተሰራ ቢገልፁም ቆጠራ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ተጀምሮ ስለመጠናቀቁ የሚያሳይ ማስረጃ ሊያሳዩን አልቻሉም፡፡ በተጨማሪም ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሲደረግ ቆጠራውን ያካሄዱት ሰራተኞች የማይገለፁና መተማመኛም የማይፈረም መሆኑ ከተለያዩ የቆጠራ ሰነዶች ለማየት ችለናል፡፡

78. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ2007 ዓ.ም አላቂ ንብረቶችን በተመለከተ ለመቁጠር ያልተቻለ ሲሆን ይህም በወቅቱ ቢን ካርድ ያልተዘጋጀና ያልቀረበ በመሆኑ ቢን ካርድ መዝጋትና ቆጠራውን ማከናወን አለመቻሉ እና ሠነዶችም ተዘጋጅተው አለመቅረባቸው፣ በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ አላቂ የፅፈትና የንፅህና ንብረቶች በተመለከተ የእቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ በተደራራቢ ሥራ ምክንያትና በህመም ምክንያት ሊገኙ ስላልቻሉ የአላቂ ንብረት ቆጠራ ማከናወን አለመቻሉ፣ በየቢሮው ውስጥ ያሉት ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር (ታግ) ያልተለጠፈባቸው ስለሆነ ንብረቶችን ለመለየት ማስቸገሩ በተጨማሪም የንብረት ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የቆጠራ ቡድኑ፣ አስቆጣሪው አካል ቢኖሩም ታዛቢ ግን አለመኖሩ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. እንዲሁም በ2004 በጀት ኣመት የዓመታዊ ቆጠራ ወቅት ድርጅቱ የማይጠቀምባቸው ያገለገሉ በርካታ ዕቃዎች መኖራቸው መታወቁና የበለጠ ከመበላሸታቸው በፊት እንዲወገዱ አስተያየት ቢሰጥም ተግባራዊ አለመሆኑ፣ የንብረት ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የቆጠራ ቡድኑ እና አስቆጣሪው አካል ቢኖሩም ታዛቢ ግን አለመኖሩ በ2005 በጀት ዓመት በንብረት ቆጠራ ቡድኑ የተዘጋጀ ሪፖርት አለመኖሩ በ2006 በጀት ዓመት በየቢሮው የሚገኙ ቋሚ

ንብረቶች ታግ ያልተለጠፈባቸው መሆኑ፣ በርካታ የድርጅቱ ቋሚ ዕቃዎች (በተለያዩ ቅርንጫፎች ጽ/ቤቶች) የሚገኙ የመለያ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ (identification no.) እና ቆጠራው ቢካሄድም የቆጠራው ውጤት ከፋይናንስ ምዝገባው ጋር የማይታረቅ መሆኑ፣ የኮርፖሬት ፕላንና ፋይናንስ ክፍል የቆጠራ ሪፖርት የማያዘጋጅ መሆኑና የቆጠራው ዉጤት ከፋይናንስና ምዝገባው ጋር የማይታረቅ መሆኑ እና የድርጅቱ ንብረት ለሆኑ ተሽከርካሪዎች ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. ይህን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በ2007 ዓ.ም ስድስት መጋዘኖች ውስጥ ቆጠራ እንዳልተከናወነና ምክንያቱ ቆጠራውን ለማከናወን የተመደቡት ሰራተኞች ስላላመነችባቸው እንደሆነና ቆጠራው በሌላ ሰው እንዲከናወን ጠይቃ እንደነበረና ሌሎች ስራዎቹዋን አቁማ ላስቆጥር ብትል አይቻልም ስለተባለች ቆጠራው በወቅቱ ሊከናወንና እስሁንም እንዳልተከናወነ ገልፃለች፡፡

81. እንዲሁም በክፍሉ የተዘጋጀው መዋቅር ከስራው ጋር የተመጣጠነ ባለመሆኑና በጣም አነስተኛ ሰው የሚያካትት የመዋቅር ጥናት በመሆኑ ያለው የሰው ሃይል ንብረቶችን እየተከታተለ መለያ ቁጥር ለመስጠትና የማስታረቁን ስራ በትክክልና ወጥ በሆነ መንገድ ሊከናወን እንዳልተቻለ ከግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ከንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪና ኦፊሰር ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ወቅት ሊታወቅ ተችሏል፡፡

82. የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ.ማ በሁሉም ግምጃ ቤቶች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ሂሳብ ክፍል ከሚገኘው ዕቃ መቆጣጠሪያ ካርድ ከግ/ቤት ከሚገኘው ቢን ካርድ ጋር ማሰታረቅ ስራ አለመከናወኑ፣ በቆጠራ የተገኘው ውጤት ከሂሳብ ክፍል መቆጣጠሪያ ካርድ ጋር እየተነጻጸረ ዓመታዊ ቆጠራው አለመከናወኑ፡፡ እንዲሁም በማዕድን ማምረት የስራ ሂደት ግ/ቤቶች ውስጥ የቋሚ ንብረት ቆጠራ በአብዛኛው ናሙና ከተወሰዱት ቋሚ ንብረቶች ውሰጥ መለያ ኮድ የተሰጣቸው ቢሆንም አንዳንድ አዳዲስ የገቡ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ኮድ አለመሰጠቱ፣ በተጨማሪም የህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት ኮድ የሌላቸው የኤክስካቬተር ዕቃዎች መለያ ቁጥራቸው ከፋይናንስ ጋር የማይገናኝ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፊያ ድርጅት ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለተዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ የማስተካከያ እርምጃ እንደተወሰደና አልፎ አልፎ መዘግየት ቢጋጥምም ምዝገባው ሣይታረቅ ሂሣብ እንዲዘጋ እንደተደረገ በተለይ ራውንድ ፓይፐን በተመለከተ ጥቆማው ትክክል እንደሆነና በተሰጠው አስተያየት መሠረት ማስተካከያ እንደተሰራለት በየመጋዘኑ ያሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ የተጠናቀቁ ምቶች፣ ቋሚ ዕቃዎችና ሌሎች ንብረቶች በርካታ በመሆናቸው ሪፖርቱ የሚዘገይበት ሁኔታ እንዳለ በቆጠራ የመጀመሪያ ረቂቅ ላይ እንደሚፈረም ሆኖም የመጨረሻው ኮፒ ለፋይንንስ ደርሦ በኮምፒውተር ተፅፎ ከተጠናቀቀ በኋላ ዋናው መተማመኛ እንደሚፈረም ሆኖም የ2006 ዓ.ም የጋራዥ ንብረት ቆጠራ ሣይፈረም እንደዘገየ ስህተቱ እንደታረመና ወደ ፊትም እንደማይደገም በተጨማሪም ቆጠራውም ከላይ ከተጠቀሰው አጋጣሚ በስተቀር መተማመኛ እንደሚፈረም ገልጸዋል፡፡

84. እንዲሁም የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አክስዮን ማህበር ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታው በሰጡት መልስ ከ20 ሺህ በላይ እቃዎችን ቅድሚያ የማስታረቅ ሥራ ማከናወን ከሁለት ወር በላይ የሚፈጅ በመሆኑ ለመተግበር አስቸጋሪ ስለሆነ የማስታረቅ ሥራው ከቆጠራ ጎን ለጎን እየተሰራ የሚገኝና ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑና የተሰጠው አስተያየት ትክክል መሆኑን እንደተቀበሉና ክፍተቱ የተፈጠረው ቀደም ሲል የተሰጠው መለያ ኮድ በቀላሉ የሚለቅ በመሆኑ እና የኮድ መስጫ ማሽኑ ደካማ ስለሆነ እንዲሁም የፊፋይናንስ ዳይሬክቶሬት በአዲስ መልክ ሌላ መለያ ኮድ ለመስጠት ስላቀደ ከፋይናንስ ጋር በመቀናጀት የማይለቅና አስተማማኝ ኮድ መስጫ ዘዴ በመምረጥ በጋራ በመቀናጀት በ2016 ለመስራት እንደታቀደ ገልፀዋል፡፡

85. በመሆኑም ቆጠራ የሚደረገውና የማስታረቅ ስራ የሚከናወነው ንብረቶቹ መኖራቸውንና በትክክል ስለመጠበቃቸው ለማረጋገጥ ሲሆን ነገር ግን ለአንዳንድ ንብረቶችና በተለይ ለተሽከርካሪዎች ቆጠራ አለመከናወኑና ከንብረት ክፍል ምዝገባ ጋር አለመታረቁ የመንግስት ንብረቶችን ለብክነት ሊያጋልጥና ለብልሹ አሰራር ሊዳርግ ይችላል፡፡

ለንብረት ስራ የሚመደቡ ሠራተኞችን በተመለከተ፣

86. ለንብረት ስራ የሚመደቡ ሰራተኞችቢቻል በሙያው ወይም ተዛማጅነት ባለው የትምህርት ዘርፍ የሰለጠኑ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

87.ሆኖም በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች ውስጥ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በመጋዘን ሃላፊና ረዳት ሃላፊ ከተመደቡት 17 ሠራተኞች ውስጥ 8ቱ በንብረትና ተዛማጅነት ባለው የትምህርት መስክ ያልሰለጠኑ መሆናቸው እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በግዥ ንብረት አስተዳደር እና በትራንስፖርት ዳይሬክቶሬት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ በመጋዘን ሃላፊ ከተመደቡት 30 ሠራተኞች ውስጥ 8ቱ በንብረትና ተዛማጅነት ባለው የትምህርት መስክ ያልሰለጠኑ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

88.በዚህም ምክንያት ንብረቶች በወቅቱና በተሟላ ሁኔታ ሊመዘገቡ እንዳልቻሉ መረጃ በሰበሰብንበትና ከባለሙያዎቹ ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማወቅ ችለናል፡፡

89.በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ሃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ላዘጋጀው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ድርጅቱ ይህን ክፍተት ለመሙላት በየጊዜው ለንብረት ሠራተኞች የውስጥ ስልጠና በመስጠት ላይ እንደሚገኝና አዲሱን መዋቀር ሲሰራም ለቦታው ተዛማጅ ትምህርት ያላቸው ባለሙያዎች መቅጠር የሚያስችል መመዘኛ እንዳሰቀመጠ ወደ ፊት በመደቡ ቅጥር ሲያስፈልግ በትምህርት ዝግጅታቸው የተሟሉ ሠራተኞችን መቅጠር የሚያስል ሁኔታ እንደተመቻቸ ገልፀዋል፡፡

90.በመሆኑም ንብረቶች በትክክልና በወቅቱ ካልተመዘገቡ የልማት ድርጅቶቹ ያሉአቸውን ንብረቶች ያሉበትን ሁኔታ አውቀው በአግባቡ እንዳይከታተሉና ለመቆጣጠር እንዳይችሉ ከማድረጉም በላይ ክፍተት በመፍጠር ለብልሹ አሰራር ሊዳርግ ይችላል፡፡

የተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች መረጃ አያያዝን በተመለከተ፣

91. የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች ለተሽከርካሪውና ለመሳሪያው የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መዝግበው ሊይዝ ይገባል፡፡

92. ይሁን እንጂ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪዎች በሰሌዳ ቁጥር የሚመዘገቡበት ሬጅስተር ተሟልቶ አለመያዝ እና ተሽከርካሪዎች ሊብሬ በሥርዓት በአንድ ቦታ ተሟልቶ አለመያዝ፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የድርጅቱ ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ያሉ መረጃዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ፣ በባንክ እዳ ለተያዙ ለ19 ተሽከርካሪዎችና ተሳቢዎች የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) ሊገኝ አለመቻሉ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. ይህን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪና ኦፊሰር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በክፍላቸው ውስጥ የሰው ሃይል ችግር ከስራው ጋር የተመጠጣነ ስላልሆነና በጣም አነስተኛ ሰው የሚያካትት የመዋቅር ጥናት በመሆኑ ያለው የሰው ሃይል ምዝገባውን ሊያከናውኑ እንዳልቻሉና እዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎችን ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን በትክክል መዝግበው እንዳልያዙና ያሉትንም ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች የተሟላ ወጥ የሆነ መረጃ የሌለ መሆኑና ወደ ፊት መመሪያዎች ሲዘጋጅና ወጥ የሆነ ፎርማት ሲዘጋጅ ምዝገባውን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡

94. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ ለተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ምዝገባ የሚያከናወነው በፋይናንስ ንብረትና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ስር በሚገኘው የንብረት አስተዳር ክፍል የድርጅቱ ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ያሉ መረጃዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ ታውቋል፡፡

95. ይህን አስመልክቶ የእርሻ መሣሪያዎች ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ሃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት

መልስ በአደረጃጀት ምክንያት በንብረት ክፍል ምዝገባው እንደማይከናወን ገልፀዋል፡፡

96.በመሆኑም ተሸከርካሪዎችና መሳሪያዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ የማይመዘገቡ ከሆነ እነዚህ ከፍተኛ ገንዘብ የያዙ የመንግስት ንብረቶች ላላስፈላጊ ብክነትና ብልሽት ከመዳረጉም በላይ ለብልሹ አሰራር ሊዳርግ ይችላል፡፡

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣

ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣

97.ቋሚም ሆነ አላቂ እቃ ለተወሰነላቸው ዓላማና ተግባር ብቻ ሊውሉ ይገባል፡፡

98. ሆኖም በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በርካታ ንብረቶች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸው፣ በንብረት አስተዳደር ቡድን መያዝና መቀመጥ ያለበት ተረፈ ምርት በየቦታው የተቀመጠ ስለሆነ ለብልሽት እየተጋለጠ መሆኑ፣ ለፈርኒቸር ስራ የሚያገለግሉ እቃዎች በህትመት መለዋወጫ እቃ ግምጃ ቤት የተገኙ መሆኑ፣ የህትመት ወረቀት መጋዝንና የመለዋወጫ ዕቃ መጋዝን ጣራቸው ባለመጠገናቸው በዝናብ ወቅት የሚያፈሱ መሆናቸው፣ የተለያዩ የካፍቴሪያ ዕቃዎች በሁለት ኮንቴይነር ውስጥ ተጠራቅመው የተወሰኑት ዕቃዎች እየዛጉ መሆናቸው ታውቋል፡፡

99. በእንጨትና ብረታ ብረት መጋዝን ውስጥ በርካታ ብረቶች በአይነታቸው ሳይለዩና በቆጠራ በማያመች መልኩ በአንድ ላይ ሆነው ወለሉ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፣ በጋራዥ መጋዝን ውስጥ በርካታየ ተለያዩ የመኪና ጉማዎች መለዋወጫ እቃዎች መኖራቸው እንዲሁም በፕሮጀክት ዕቃግ ምጃ ቤት ለ20 ዓመት ተቀምጠው የነበሩ የተለያዩ ንብረቶች ለት/ምቤቶች እየተሰራጩ የሚገኙ ቢሆንም አሁንም በርካታ ንብረቶች መኖራቸዉ፣ የጅብሰም ድንጋይ መጋዝን ከሌላው መጋዝን አንፃራዊ ሲታይ በከፍተኛ ሁኔታ ዝናብ እያስገባ መሆኑ፣ በፕሪንቲንግ ክፍል ያለው ጣሪያ እያፈሰሰ መሆኑና በተለያዩ ክፍሎች መስታወቶች መሰበራቸው በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

100. ይህን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የፕሮጀክት ንብረቶችን በተመለከተ ለብዙ ጊዜ ተቀምጠው መቆየታቸው ይታወቃል በአሁኑ ወቅት ግን ባለሙያ ተቋቁሞ ወደ ስራ ለመግባት እና ቤቱም ተሰርቶ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው ከዚህ ውጪ ያሉት የፕሮጀክት እቃዎች ማለትም የተለያዩ የስፌት መኪናዎች፣ የሹራብ መስሪያ ማሽኖችና የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች እና የተለያዩ የፕሮጀክት እቃዎች ለማስወገድ በሂደት ላይ እንዳሉና በተጨማሪም በፕሪንቲንግ ክፍል ያለው ጣሪያ እያፈሰሰ መሆኑና በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ መስታወቶች መሰበራቸውን በተመለከተ ለተጠየቁት በሰጡት መልስ ክፍሉ በደብዳቤ ስላሳወቃቸው ችግሩ ያልተቀረፈ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

101. በተጨማሪም የተለያዩ የብረት ቁርጥራጦች የሚሸጡ ስለሆነ እዚህም እዚያም ተቀምጠዋል አንዶንዶቹ ግን የምስቀመጫ መጋዘን ጥበት ስላለ በየቦታው ወድቀው እንደሚገኙ ነገር ግን ወደ ፊት መጋዘን ከተሰራ እዛ ለማስቀመጥ እንደታሰበና በየቦታው ወድቀው የሚገኙ መኪናዎች ከድርጅቱ ውጪ እንደሆኑና የትምህርት ሚኒስቴር የነበሩ እንደሆነና ለጥገና የመጡ እንደነበር ታርጋ ቁጥር ያላቸውም የሌላቸውም እንዳሉና በተደጋጋሚ ጊዜ ለአስወጋጅ ኮሚቴና ለተቆጣጣሪው አካል እንዳሳወቁ እና የኤፌድሪ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ይወስዳቸዋል ተብሎ እስካሁን ቆመው እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

102. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በድርጅቱ ንብረቶች ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ ተደርገው ለሚፈለገው ስራ በትክክል ለታለመለት ዓላማ መዋላቸውን የሚረጋገጥበት የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት የሌለ በመሆኑ የታቀዱት ሥራዎች ተጠናቀው ንብረቶች ተርፈው ሲመለሱ በምን ላይ ተመዝግበው እንደሚያዙና ለቀጣይ ስራዎች እንዴት እንደሚውሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ንብረቶችን በሃላፊነት የሚረከባቸው አካል ሳይኖር በድርጅቱ ግቢ ውስጥ ፀሃይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ተቀምጠው ለብልሽትና ብክነት በተጋለጠ ሁኔታ እንደሚገኙ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

103. በአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ ኢ.ማ ከጣና በለስ ፕሮጀክት በኢኮኖሚ ልማት አማካኝነት በስጦታ የተገኘ ፊያት ኦኤም መለስተኛ የጭነት መኪና በሚቾልኮትስ

ኩባንያ ለጥገና ጋራዥ ገብቶ አምስት አመት ያስቆጠረ (ታህሳስ 30, 2001 የገባ) በክትትል ማነስ እስከ ጥር 2006 ዓ.ም ድረስ ተጠግኖ ሳይወጣ የቆየ መሆኑና ሞተሩ (ቁጥር 336012 የሻንሲ ቁጥር 001597) የት እንደደረሰ የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

104. ጉዳዩን አስመልክቶ የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ/ማህበር ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ የተሰጠው አስተያየት በከፊል ተቀባይነት እንዳለውና ለችግሩ መፍትሔ ለመፈለግ አ/ማህበሩ ጉዳዩን ወደ ህግ የወሰደው ቢሆንም ኩባንያው ችግሩን በድርድር ለመፍታት ያቀረበውን ሃሳብ አ/ማህበሩ ተቀብሎ ድርድሩን ለማካሄድ ኮሚቴ እንደተቋቋመና በተያያዘም ጠፋ የተባለው ሞተር ያልጠፋና በኩባንያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ እንደሆነና የጎደሉት ጥቃቅን የሆኑ የሞተር ክፍሎች መሆናቸው ስለተረጋገጠ በአሁኑ ወቅት የመኪናውን ርክክብ ለመፈፀምና ወደ አ/ማህበሩ ቅጥር ግቢ ለማጓጓዝ ስራው እየተጠናቀቀ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

105. በኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር ዋጋ ያልወጣላቸው፣ ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ቢጠገኑ ወደ ሥራ ሊገቡ የሚችሉ፣ ያገለገሉ ጊዜ ያለፈባቸው አላቂና ቋሚ ንብረቶችን በክምችት ተይዘው የሚገኙ መሆኑ፣ በተለያዩ የድርጅቱ መጋዝኖች እና በየረር ጠጠር ማምረቻ ልዩ ልዩ አላቂ የሚገኝ ዕቃዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከፊሉም ወዳድቆ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት ከአ/ማህበሩ ንብረቶች መጥፋታቸው ታውቋል፡፡

106. ጉዳዩን አስመልክቶ የኮስቲክ ሶዳ አ/ማህበር ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ፋብሪካው ሲተከል ከቀድሞ የሶቬይት ህብረት የገቡ በርካታ የፋብሪካ የመለዋወጫ እቃዎች ዋጋ የሌላቸው በብዛት የሚገኙ እንደሆነና ዋጋ ተተምኖላቸው ለመመዝገብ ጥረት ቢደረግም ተመሳሳይ ዕቃዎች በገበያው ላይ የሌሉ በመሆኑ ዋጋቸውን ማግኘት እንዳልተቻለና በ2006 በጀት ዓመት የማያገለግሉትን ጨረታ በማውጣት በመሸጥ ብር 1 ሚልየን ማግኘት የተቻለ እንደሆነና ወደፊት ሊያገለግሉ የሚችሉትን በገበያ ዋጋ ለመመዝገብ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ፣ በብልሽት አገልግሎት የማይሰጡትን ንብረቶች በመለየት በ2008 ዓ.ም በሽያጭ ለማስወገድ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ እንዲሁም ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ጥበቃዎች በአዲስ መልክ እንዲደራጁ እንደተደረገና

ቀደም ሲል በግቢው ውስጥ ተበታትነው የነበሩትን ንብረቶች ሁሉ ወደ መጋዘን እንዲቀመጡ በመደረጋቸው ስርቆትን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ እንደተቻለ ገልፀዋል፡፡

107. በመሆኑም እነዚህ ንብረቶች በትክክል አለመጠበቃቸው የመንግስት ንብረት ጉዳት ሊደርስበት፣ ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍትና ከዚህም በላይ መንግስትን ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡

ለቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና መገባቱን በተመለከተ፣

108. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ኢንሹራንስ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና ሊገቡላቸውና የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ ሊያዘጋጁላቸው ይገባል፡፡

109. ሆኖም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የድርጅቱ ጋራዥ እስከ 2006 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ የመድን ሽፋን ያልተገባለት መሆኑ፣ ለበርካታ ዓመታት በብልሽት ለቆሙ ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን የተገባላቸው መሆኑ፣

ለምሣሌ፡-

- ✓ የታርጋ ቁጥሩ 3-09077 ሬኖ 19 አውቶሞቢል በ23/10/89 የገቢ ሰነድ የተቆረጠለት ተሽከርካሪ፣
- ✓ የታርጋ ቁጥሩ 3-12668 ሬኖ 19 አውቶሞቢል በ23/10/89 የገቢ ሰነድ የተቆረጠለት ተሽከርካሪ እንዲሁም የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

110. ስለጉዳዩ ከግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የኢንሹራንስ ቡድን መሪ ጋር በተደረገው ውይይት እነዚህ ተሽከርካሪዎች በንግድ ባንክ የብድር ዕዳ መያዣነት የተያዙ ስለሆነ ከድርጅቱ በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት ምንም እንኳን ለብዙ ጊዜ አገልግሎት መስጠት አቁመው የቆሙ ቢሆንም እንደሆነና የመድን ሽፋን የተገባላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

111. በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ድርጅቱ ለማስፋፍያ ስራ የሰራቸውን ግንባታዎች የመድን ሽፋን ያልተገባላቸው መሆኑ እና ለድርጅቱን

ብረቶች የመድን ዋስትና ሽፋን ሲገባላቸው የንብረቶችን ዋጋ ከድርጅቱ ፋይናንስ ሰነድ ጋር ያልተገናዘበ መሆኑ ታውቋል፡፡

112. ይህን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የፋይናንስ ስራ አስፈፃሚ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የ2008 ዓ.ም ለሁሉም የመድን ዋስትና ክፍያ እንደተከፈለና ሰነዱም እንዳለ እንደውም ኢንሹራንስ የተገባው ከቡና ኢንሹራንስ አ/ማ ጋር እነደሆነ ነገር ግን ከዛ በፊት ስለነበረው ሁኔታ ድርጅቱ ውስጥ ስላልነበሩ እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

113. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ድርጅት የድርጅቱ መሣሪያዎች ለሆኑ ዶዘር፣ ግሬደር… ኢንሹራንስ ያልተገባላቸው መሆኑ፣ በአ/ማህበሩ ውስጥ እያሉ (ጥገና ላይ ሊሆን ይችላል አንዳንዶቹ) ነገር ግን የመድን ሽፋን ያልተገባላቸው በቁጥር 14 የሆኑ ተሽርካሪዎች መኖራቸው፣

ለምሣሌ ያህል፡-

- ✓ ታርጋ ቁ. 3-67769 የሆነ አነስተኛ ተሽከርካሪ፣ ታርጋ ቁ. 3-10077 የሆነ ኒሳን፣ 3-19806 የሆነ ኒሳን፣ ታርጋ ቁ. 3-10786 የሆነ ቮልቮ፣
- ✓ በአ/ማህበሩ የመድን ሽፋን ተገብቶላቸው ነገር ግን በትራንስፖርት ክፍል በተዘጋጀው የ2008 ዓ.ም የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ሪፖርት ውስጥ ዝርዝራቸው የሌሉ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው ለመጥቀስ ያህል ታርጋ ቁ. 3-21046 የሆነ ኒሳን ፒክ አፕ፣ ታርጋ ቁ. 3-12285 የሆነ ስካኒያ ትራክ፣ 3-46543 ኢቬኮ ትራክ እንዲሁም የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

114. ይህን አስመልክቶ ከእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ድርጅት የኢንሹራንስ ኦፊሰር ጋር በተደረገ ውይይት ለዶዘሮችና ግሬደሮች መድን ሽፋን እንዳልተገባላቸውና ምክንያቱ ብዙም አደጋ የማያደርሱ ስለሆነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለንብረቶች መለያ ቁጥር መሰጠቱን በተመለከተ፣

115. በመንግስት ልማት ድርጅት የሚገኝ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ሊሰጠውና የመለያ ቁጥሩ በቋሚ ንብረቱ ላይ ሊፃፍ ወይም ሊለጥፍ ይገባል፡፡

116. ሆኖም ትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር መስጠት ቢጀመርም ያልተጠናቀቀ መሆኑ፣ የድርጅቱ ቋሚ ንብረቶች

መለያ ኮድ እንዲሰጣቸውና በመዝገብ ላይ ንብረቱ የሚገኝበት ክፍልና ተጠቃሚው ማን እንደሆነ ስለማይገልፅ ዕቃውን በአካል መገኘታቸውን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ መዝገብ ላይ የዕቃዎች መለያ ቁጥር እና የንብረቱ ተገልጋይ ስም ባለመኖሩ ናሙና ወስዶ ስለ አጠባበቅ እና አያያዙ ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ እንዲሁም አዲስ ቋሚ ዕቃዎች ሲገዙ በወቅቱ መለያ ቁጥር የማይሰጣቸው መሆኑ ለምሳሌ በ2004 በጀት ዓመት አዲስ የተገዙ የኮምፒውተር እና ፕሪንተሮች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ እንዲሁም ምዝገባው ከቆጠራ ጋር እንዲታረቅ ለማስቻል የቆጠራ ስራ የተጀመረ ቢሆንም ስራው አለመጠናቀቁ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

117. ጉዳዩን አስመልክቶ የድርጅቱ የፋይናንስ ሥራ አስፈፃሚ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአብዛኛው መለያ ቁጥር ቢሰጣቸውም ያልተሰጣቸው ካሉ የማየት ስራ እንደሚሰሩና ጥቂት ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑና እስከ መስከረም 30 2008 ዓ.ም ድረስ ለሁሉም ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር እንዲሰጥ የጊዜ ሰሌዳ እንደተያዘ ገልፀዋል፡፡

118. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ2007 በጀት ዓመት በ3ኛው ሩብ ዓመት ቋሚ ንብረቶችን በመለያ ቁጥርና በቦታ እንዲሁም ተሽከርሪዎች በሰሌዳ ቁጥር የሚመዘገቡበት ሬጅስተር ተሟልቶ አለመያዝ በተጨማሪም በርካታ በዋናው መ/ቤትና በተለያዩ ቅርንጫፍ ቢሮዎች የሚገኙ የድርጅቱ ቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ.ማ ህንጻዎች፣ ኮንቴይነሮች፣ መኪናዎች፣ የቢሮ ዕቃዎች እና ሌሎች የአክሲዮን ማህበሩ ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥሮች (i.d nos) እንዲሰጣቸው በተለያዩ ጊዜያት ሪፖርት ቢደረግም ተፈጻሚ ሊሆን አለመቻሉ ታውቋል፡፡

119. ጉዳዩን አስመልክቶ የድርጅቱ የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪና ኦፊሰር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በድርጅቱ የተዘጋጀው መዋቅር ከስራው ጋር ያልተመጣጠነ በመሆኑና በጣም አነስተኛ የሰው ሃይል ስላለ ቋሚ እቃዎችን እየተከታተለ መለያ ቁጥር ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሆነ በዋናው መስሪያ ቤትና በቅርንጫፍ ቢሮ ለሚገኙት ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ሰጥተው እንዳልጨረሱ ገልፀዋል፡፡

120. በተጨማሪም የግዥ፣ ንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ በሰጡት መልስ ለቋሚ ንብረቶች ቁጥር መስጠት ስራ ተጀምሮ መለያ ቁጥር መስጫ ማሽኑ በመበላሸቱ ምክንያት ስራው ተቋርጦ እንደነበርና በአሁኑ ወቅት ግን የማሽኑ ግዥ ለመፈፀም እንቅስቃሴ የተጀመረ ስለሆነ ግዥውን በመፈፀም ስራው በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

121. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ድርጅት ከህንፃዎች ውስጥ የጀኔሬተር ቤትና የበር ላይ የጥበቃ ቤቶች መለያ ቁጥር እንዳልተሰጣቸው፣ በጥገና የሚገኙ ትክል ማሽነሪዎች በካይዘን ትግበራ ወቅት በቀለም በመቀባታቸው ቁጥራቸው መጥፋቱ፣ በአጠቃላይ የንብረቶች ቁጥር የተፃፈው በማርከር በመሆኑ በቀላሉ ሊጠፉ ሊሰረዙና ሊለወጥ የሚችል መሆኑ፣ ለአንዳንድ ንብረቶች መለያ ኮድ ያልተሰጣቸው መሆኑ ለምሳሌ ያህል ለአድሚኒስትሬሽ ክፍል ለጀነሬተር እና ለኮንቴነር በፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ክፍል ለኮንቴነሮች መለያ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

122. ጉዳዩን አስመልክቶ የድርጅቱ የንብረት አስተዳደር ሃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሁኔታው ትክክል መሆኑን ገልፀው ህንጻዎች የምንለየው በስማቸው እንደሆነና መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

123. በመሆኑም ለንብረቶች መለያ ቁጥር ካልተሰጣቸው የመንግስት ንብረት ሊጠፉ፣ ሊለወጥና ለስርቆት ሊዳረግ ይችላል፡፡

ንብረቶችን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከል ተስማሚ የንብረት መጋዘን መኖሩን፣

124. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረታቸውን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከልና ተስማሚ የንብረት መጋዘን ሊኖራቸው ይገባል፡፡

125. ይሁን እንጂ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የህትመት ወረቀት መጋዘንና የመለዋወጫ ዕቃ መጋዘን ጣራቸው ባለመጠገናቸው በዝናብ ወቅት የሚያፈሱ መሆናቸው፣ የጅብሰም ድንጋይ መጋዘን በከፍተኛ ሁኔታ ዝናብ እያስገባ መሆኑ፣ በፕሪንቲግ ክፍል የሚገኘው ጣሪያ የሚያፈስ መሆኑና በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ መስታወቶች የተሰበሩ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

126. ይህን አስመልክቶ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በፕሪንቲንግ ክፍል ያለው ጣሪያ እያፈሰሰ መሆኑና በተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ መስታወቶች መሰበራቸውን በተመለከተ ለተጠየቁት በሰጡት መልስ ክፍሉ በደብዳቤ ስላሳሳወቃቸው ችግሩ ያልተቀረፈ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

127. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች በመጋዘን አካባቢ ያለመኖርና ያሉትም ካሊብሬት በወቅቱ የማይደረጉ መሆኑ፣ የድርጅቱ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በ20/9/2014 ካሊብሪት መደረግ ቢኖርበትም ያልተደረገ መሆኑ፣ በምልከታ ወቅት በአሮጌ የመለዋወጫ ንብረቶች ማስቀመጫ መጋዘንበርና ኬሚካሎች የሚቀመጡበት የድርጅቱ መጋዘኖች ላይ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ያለመኖራቸው፣ የአደጋ ጊዜና የንብረት መጥፋት በሚያጋጥምበት ወቅት የሚያገለግሉ ስልኮችም ሁሉም ሰው በሚያያቸው ቦታ ያልተለጠፉ መሆኑ፣ በሰሜን ምስራቅ ሸያጭና ስርጭት ማዕከል በደሴ ማ/ማ/መጋዝን በቀን 19/6/2006 ዓ.ም በተፃፈ የሪፖርት ውጤት መግለጫ ቅፅ በዚህ መጋዝን የመጋዘኑ ጣሪያ ንፋስ አንስቶት በዝናብ ምክንያት ንብረቶች እየተበላሹ መሆኑ ታውቋል፡፡

128. ጉዳዩን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በየሳምንቱ ስብሰባ ላይ ጉዳዩን እንደሚያነሱትና ነገር ግን ችግሮቹን ሃላፊዎቹ በቃል ብቻ ከማወቅ በአካል መጥተው እንዳላዩት የኮንስትራክሽንና የጥገና አማካሪ ቡድን ችግሩ እንደተነገረውና እስካሁን መፍትሔ ሊሰጥ አለመቻሉ በዚህም ምክንያት በስራቸውና በጤንነታቸው ላይም ችግር እየፈጠረባቸው እንዳለ ገልፀዋል፡፡

129. በተጨማሪም የግዥ፣ ንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ በሰጡት መልስ በዋናው መ/ቤትና መጋዘን አካባቢ ያሉ እሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች በአሁኑ ወቅት ካሊብሬት እንደተደረጉና ሆኖም አስፈላጊ በሆኑ ተጨማሪ ቦታዎች በመፈተሽ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች እንደሚቀመጡና በእሳት አደጋ ጊዜና በንብረት መጥፋት ወቅት የሚያገለግሉ ስልኮችም ማንም ሰው በሚያየው ቦታ እንዲለጠፍ እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

130. በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ በዋናው ግምጃ ቤት ለአንዳንድ ንብረቶች ታግ ያልተለጠፈላቸው መሆኑ ለዚህም ምክንያት ተጨማሪ ወጪ

ይፈጥራል በሚል እንደሆነና ለአንዳንድ ንብረቶች የተለጠፉ ቢን ታግም ላይ ዕቃዎቹ ስንት እንደሆነ ቁጥራቸው የማይገለፅ መሆኑ እንዲሁም ጣሪያው ሦስት ቦታዎች ላይ የሚያፈስ መሆኑና የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለው መሆኑ በተጨማሪም በፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ስር በሚገኘው መጋዘን ለንብረቶች ቢን ታግ እንዳልተለጠፈባቸውና የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያም የሌለ መሆኑ ለዚህም ባለሙያዎቹ እንደገለጹት ንብረቶቹ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ስለሚቀመጡ ታግ እንደማይለጠፍባቸው ገልፀዋል፡፡

131. በህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት በቁጥር 1 ምርት ጣቢያ የሚገኙ መጋዝኖች (ኮንቴነሮች) ጣሪያቸው የሚያፈስ ስለሆነ በንብረት ላይ ብልሽት እየታየ መሆኑ፣ አንዳንዶቹ መጋዝኖች ለመክፈትና ለመዝጋት ስለሚያስቸግሩ በውስጡ የሚገኘውን ንብረት በቀላሉ ለማውጣት የማይቻል መሆኑ፣ እነዚህ መጋዝኖች መብራት የሌላቸው ስለሆነ በውስጣቸው የሚገኙትን ንብረትም ሆነ ቢን ካርድ ለማውጣትም ሆነ ለማስቀመጥ ችግር መፈጠሩ ታውቋል፡፡

132. በመሆኑም የድርጅቶቹ ንብረቶች የሆኑት መጋዘኖች በአፋጣኝ ጥገና ካልተደረገላቸው የመንግስት ንብረት ለብልሽት ሊዳረግ ይችላል፡፡

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣

የንብረት አወጋገድን በተመለከተ፣

133. እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ባሉበት ሁኔታ በመሸጥ ወይም መለዋወጫቸውን ፈትቶ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በውዳቂ ብረታ ብረትነት በወቅቱ እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡

134. ሆኖም በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የድርጅቱ ንብረት ያልሆኑ መኪናዎች ለብዙ ጊዜ በጋራዥ የነበሩ በመሆናቸው ለኢፌዲሪ ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ እንዲሰጡ የተወሰኑ ቢሆንም አለመተግበሩ፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው የተለያዩ ኬሚካሎች መኖራቸው፣ በድርጅቱ ዉስጥ ለረጅም ጊዜ በብልሽት ቆመው የሚገኙና በአሁኑ ወቅት አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ

የህትመት የፈርኒቸር ማምረቻዎች መኖራቸው ለመጥቀስ ያህል 17 የህትመት መሳሪያዎችና 31 የፈርኒቸር ማምረቻ ማሽኖች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆዩና በቀጣይም አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሆናቸውና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ያልተወገዱ መሆናቸው፣ በፕሮጀክት ዕቃ ግምጃቤት ብዙ ዓመታት ተቀምጠው የነበሩ የትምህርት መሳሪያዎች ለት/ም ቤቶች እየተሰራጩ የሚገኙ ቢሆንም አሁንም በርካታ ንብረቶች መኖራቸዉ፣ በቆጠራ የተገኙ ያገለገሉና የተበላሹ በተደጋጋሚ አመታት የማይንቀሳቀሱ ለሥራ ግብአት ሊሆኑ የማይችሉ ንብረቶች መኖራቸው፣

ለመጥቀስ ያህል፡-

- ✓ ኮድ ያላቸው ከ1-23 በዝርዝር የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች፣
- ✓ ኮድ የሌላቸው ከ1-80 በዝርዝር የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች፣
- ✓ 16-01-0538 ኒትሪክ አሲድ ብዛት 5 ለብዙ ዘመናት የተቀመጠ፣
- ✓ አታሚና አሳታሚ ዳይሬክቶሬት የሚጠቀምባቸው ወደ 66 የሚጠጉ ማሽኖች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 21 አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ጥገናም ቢደረግላቸው ማምረት የማይችሉ መኖራቸውና ያልተወገዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

135. ጉዳዩን አስመልክቶ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በቅርቡ ለአስወጋጅ ኮሚቴ ደብዳቤ እንደፃፉና ደብዳቤው በእጃቸው እንዳለ በፊት የአስወጋጅ ኮሚቴ የሚባል እንዳልነበረና የግዢ ኮሚቴ ይባል እንደነበረና ስራዎችም በዚሁ ስር ይሰሩ እንደነበረ ነገር ግን በአዲሱ አወቃቀር መሰረት የአስወጋጅ ኮሚቴ ስለተቋቋመ በዚሁ ደብዳቤ ማሳወቃቸው ለብዙ ዓመታት የተቀመጠ ስለተባለው ኒትሪክ አሲድ ባለ 200 ሊትር ብዛት አምስት ሲሆን ኬሚካል ስለሆነ በነሱ ደረጃ እንደማይወገድና በፅሁፍ ባይሆንም በስልክ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተሄደበት እንደሚገኝ ስለማይሰሩ ማሽኖችን በተመለከተ ጥቂቶች ቢሸጡም ያልተሸጡ በርካታዎችን በ2008 ዓ.ም ለመሸጥ እንደታሰበ ገልፀዋል፡፡

136. በተጨማሪም ለብዙ ጊዜ ጋራዥ ቆመው ስላሉ ተሽከርካሪዎች የትምህርት ሚኒስቴር ተሽከርካሪዎች እንደሆኑና የድርጅቱ ጋራዥ ለጥገና የመጡ የነበሩ ሲሆን

ታርጋ ቁጥር ያላቸውና የሌላቸው እንዳሉ ከተቆጣጣሪው ኤጀንሲው ጋር ተፃፅፈው ለኢፌዲሪ ብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ እንዲሰጡ ተብሎ እስካሁን ድረስ ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ቆመው እንዳሉ መቼ እንደቆሙና የትኞቹ ታርጋ እንደሌላቸውና እንዳላቸው ግን መረጃው የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

137. እንዲሁም በፊርኒቸርና ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማምረቻ 211 የሚጠጉ ማሽኖች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከ1-34 በዝርዝር የቀረቡት ጥገና ቢደረግላቸውም የማይሰሩ ሲሆን ነገር ግን ያልተወገዱ መሆናቸው፣ ያለአገልግሎት ለረጅም ዘመናት (ከዛሬ 25 ዓመታት በፊት የተገዛ) የቆየ የጡብ ማምረቻ ማሽንና በርካታ ንብረቶች በመጋዘኖች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ማሽኖችና የቢሮ መገልገያና ቁሳቁሶች መኖራቸው በተጨማሪም የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ሁለት ፎርክሊፍቶች መኖራቸው፣ በመገጣጠመያ ክፍል ተመርተው እና ተጠናቀው ያበቁ ምርቶች በማምረቻውን ወለል መቀመጣቸው ታውቋል፡፡

138. በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ2004 በጀት ዓመት ለረዥም ጊዜ ያገለገሉ 4 የጭነት መኪናዎች በሽያጭ እንዲወገዱ በዕቅድ ተይዞ እንዲወገድ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ ውጭ ያልተወገደ መሆኑን፣ አሮጊ ንብረቶችን ወጥነት ባለው መልኩ በሰነድ መዝገብ በመያዝ በወቅቱ የሚወገዱበት ስርዓት አለመኖር እና ጊዜ ያለፈባቸውን በወቅቱ አለማስወገድ፣ በድርጅቱ አንዳንድ የእቃ ግምጃ ቤቶች በሰነድ ሳይያዙ የተቀመጡ ልዩ ልዩ ዕቃዎች መኖራቸው፣ በአሮጊነት የተመዘገቡት ደግሞ ወጥ በሆነ መልኩ ቢን ካርድ የሌላቸው መሆኑ፣ የአሮጊ ዕቃዎች አወጋገድ አዝጋሚ በመሆኑ ምክንያት ለረጅም ጊዜ የቆዩ የተለያዩ ዕቃዎች ተከማችተው መገኘታቸው ታውቋል፡፡

139. እንዲሁም አዳዲስ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች መ/ቤቱ ለወደፊቱ ሊጠቀምባቸው የማይችሉ ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳይኖራቸው በእቃ ግምጃቤት ውስጥ በየአመቱ እየተቆጠሩ የሚቀመጡ መሆኑ ለማሳያ ከ1997 በኃላ ወጪ ያልሆኑ fuel filter Assey part no. 3418624 የአንዱ ዋጋ 432.58 ብዛት 110*432.58=47583.35 ፣ በ30/10/2000 በኃላ ወጪ ያልሆነ water lose part no. 42040228 የአንዱ ዋጋ 91.48 ብዛት

227*91.48=20765.96 እና በ30/4/2001 በኃላ ወጪ ያልሆነ Air filter part no. 1901825 የአንዱ ዋጋ 209.40 ብዛት 137*209.40=28687.80 ታውቋል፡፡

140. ጉዳዩን አስመልክቶ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የእቃ ግምጃ ቤት ሃላፊ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ አሮጌ ዕቃ ማስቀመጫ መጋዝ ውስጥ ለሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ነገር ግን ሊሸጡ እንዳልቻሉ መጋዘን ውስጥ ያሉ እቃዎች ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን የተረከቧቸው በርክክብ ቬርባል እንደሆነ ምዝገባም ያልተከናወነላቸው መሆኑን ንብረቶች ወደ አሮጌ እቃ ማስቀመጫ ሲገቡም የሚሰሩና የማይሰሩ ተብለው በባለሙያ ተለይተው እንደማይመጡ ገልጸዋል፡፡

141. በተጨማሪም የግዥ፣ ንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ በሰጡት መልስ ለአሮጌ ዕቃዎች ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ እንደሚያዝ ሆኖም አልፎ አልፎ ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ላልተዘጋጀላቸው እንዲዘጋጁ እንደሚደረግና አሮጌ ንብረቶች በሰነድ ተመዝግበው እንዲያዙ እንደሚደረግ ችግሩ ግን ለተደጋጋሚ ጊዜ ጨረታ ቢወጣም ገዥ በመጥፋቱ እንዲሁም በመመሪያው መሠረት ለተለያዩ አካላት ስጦታ በመስጠት ለማስወገድ ቢሞከርም ፈላጊ በማጣታቸው ለማስወገድ እንዳልተቻለና ወደ ፊት ንብረቶችን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

142. እንዲሁም በእርሻ መሣሪያዎች ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ በፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ሥር በርካታ ተሽከርካሪዎች (ትናንሽ መኪናዎች እና ሰርቪሶች) ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸውና ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ ያልተወገዱ መሆናቸው እንዲሁም አንድ አይፋ መኪናና ከ5 በላይ የሆኑ ዶዘርና ግሬደር ያልተወገዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

143. ይህን አስመልክቶ የድርጅቱ ሃላፊዎች በመውጪያ ስብሰባ ከክሊኒኩ ጀርባ ያሉት ተሽከርካሪዎች የባለ አደራ ቦርድ እንደሆኑ አ/ማ እንደገና ሲዋቀር በ1994 ዓ.ም ለባለ አደራ ቦርድ የተሰጡ እንደሆነና ከዚህ በኋላ ሊወገዱ የማይችሉና ወደ ማቅለጫ መሄድ እንዳለባቸውና 3 ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ሊሸጡ ያለመቻላቸውና በ1994 ዓ.ም ሲረከቧቸው የማያገለግሉና የማይሰሩ እንደነበሩ በተጨማሪም ተሽከርካሪዎቹ በፋይናንስ፣ ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ስር እንደማይገኙና ሂሳባቸውም የተያዘው በባለ አደራ ቦርድ እንደሆነ ገልፀዋል ሆኖም በድርጅቱ ግቢ

ውስጥ እያሉ በሃላፊነት ተሽከርካሪዎቹን የሚጠብቃቸው ክፍል አለመኖሩ ተገቢ አይደለም እንዲሁም ድርጅቱ ተሽከርካሪዎቹንና አይፋ መኪናውን ሲረከብ የሚያገለግሉ እና የሚሰሩ እንደነበሩ መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

144. በአሰላ ብቅል ፋብሪካ አገልግሎት የሰጡ ዕቃዎች በሽያጭ በወቅቱ ያልተወገዱ መሆኑ፣ እንዲሁም የህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት ሊወገድ የሚገባው አሮጌ መልቲ ብሎክ ማሽን መጋዝን ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በተጨማሪም የተሰባበሩ የቢሮ ዕቃዎች ማለትም ጠረጴዛ ወንበርና መደርደሪያ በመጋዝን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

145. በተጨማሪም በኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ.ማ በ2006 በጀት ዓመት በላብራቶሪ ዋና ክፍል እና ልዩ ስሙ ደረቅ ጣቢያ (ሻኪሶ) ተብለው በሚጠሩ ግ/ቤቶች ውስጥ ለድርጅቱ ግልጋሎት የማይሰጡ እና ጊዜ ያለፈባቸው 4241 ላይን አይተም መለዋወጫዎች በየዓመቱ ቆጠራ የሚደረግ መሆኑ፣ ለብዙ ዓመታት ጥቅም ሳይሰጡ ቆመው ያሉ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውና ቦርዱ ተሽከርካሪዎቹ በአስቸኳይ እንዲወገዱ መመሪያ መስጠቱ፣ በጉለሌ እና ንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ፋብሪካ ንብረት መጋዘን ውስጥ ከ10 ዓመት በላይ በስራ ላይ አገልግሎት የማይሰጡ እንቅስቃሴያቸውን ያቆመ የተለያዩ መኪናና የማሽነሪ መለዋወጫዎች በብዛት በመጋዘን ውስጥ ተደርድረው የሚገኙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

146. እንዲሁም ንብረቶቹ በተደጋጋሚ ጊዜ እንዲወገዱ ጨረታ ወጥቶባቸው ያልተሸጡ በመሆናቸውና ለረጅም ጊዜ በስቶር ውስጥ በመቀመጣቸው የስቶር መጣበብ ከመፍጠሩም ሌላ የንብረት አስተዳደር ስራውን ለመስራት ችግር መፍጠሩ፣ በማዕከላዊ ላብራቶሪ ያሉ ብዛታቸው ከ 45 በላይ የሆኑ ማሽነሪዎችን የመለየት የጨረታ መነሻ ዋጋ የማውጣትና የማስወገጃ መንገዶችን የመለየት ስራ በበጀት ዓመቱ 100% ለማድረግ ቢታቀድም ምንም ነገር ያልተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

147. ጉዳዩን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ልማት ማዕድን አ/ማህበር ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ የተሰጠው አስተያየት ትክክል እንደሆነና ቀደም ሲል ንብረቶቹን ለማስወገድ በቦርድ የተቋቋሙት የአስወጋጅ ኮሚቴ ሃላፊዎች በተለያዩ ምክንያቶች ስለተቀያየሩና በተቀመጠው መርሃ ግብር መሰረት ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሃሳብ ባለማቅረባቸው በ2007 ዓ.ም በ4ኛው ሩብ ዓመት መጨረሻ ላይ የተቋቋመው አዲስ ኮሚቴ በአዲስ መልክ

በመጀመሩ ከባድና ቀላል ተሽከርካሪዎች፣ ከባድ መሣሪያዎች፣ ያገለገሉ ጎማዎችና ባትሪዎች፣ የቢሮ ፈርኒቸሮች እንዲሁም የቢሮ ኤሌክትሮኒክስ እንዲለዩና የጨረታ መነሻ ዋጋ በመተመን ጨረታ እንዲወጣ በማድረግ ከ2.5 ሚልዮን ብር በላይ ሽያጭ ለማከናወን ለገዥዎች የአሸናፊነት ደብዳቤ እንደተሰጠና በ2015 የመጨረሻ ሩብ ዓመት ከ10 በላይ መኪናዎች በጨረታ እንዲወገዱ ሂደቱ እያለቀ እንደሆነና መረጃ ያልተሞላላቸውን የማሟላት ሥራ እየተሰራ እንደሆነና በ2016 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለማስወገድ እቅድ እንደተያዘ ገልፀዋል፡፡

148. በፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት አገልግሎት የማይሰጡ የድርጅቱ ንብረቶች ተለይተው በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ 10 በዕቅድ ተይዞ አምስት ብቻ የተወገዱ መሆኑ፣ እንዲሁም በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ዘገምተኛ እንቅስቃሴ ያላቸው ብር 161,311.25 ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው ብር 35,291.65 የተበላሹ ብር 20,148.64 ያላቸው ንብረቶች ቢኖሩም በየጊዜው የማስወገድ እርምጃ አልተወሰደም፣ በጊዜ ብዛትና ሞዴል መለዋወጥ የማይንቀሳቀሱ የመካኒካል መለዋወጫዎች ግምታቸው ብር 180,364.39፣ የኤሌክትሪካል ዕቃዎች ግምታቸው ብር 88,552.44 የሆነና ፈጽሞ እንቅስቃሴ የሌላቸው (dead stock) ተብለው ተመዝግበው የሚገኙ ብር 43,469.46 ግምት ያላቸው የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ያልተወገዱ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

149. ጉዳዩን አስመልክቶ የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት ሃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ በሰጡት መልስ ንብረቶች እንዲወገዱ ሲደረግ ከመዝገብ ዋጋቸው በታች በሚሆኑበት ጊዜ በተደጋጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ስለሚደረግ በወቅቱ ያልተወገዱ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት ግን ንብረቶቹ በሽያጭ እንዲወገዱ እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡

150. በመሆኑም ገንዘብ ወጥቶባቸው መንግስት የገዛቸው ንብረቶች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ ስለሆነ እነዚህ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ አፋጣኝ መፍትሔ ካልተወሰደ የመንግስት ንብረት ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎችን በተመለከተ፣

151. የልማት ድርጅቶች የሚወገዱ ንብረቶች በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች ወይም መድሀኒቶች ወይም የጨረር ጉዳት የሚያስከትሉ ሆነው ሲገኙ በአወጋገድ ላይ አስፈላጊውን እገዛ ከሚመለከተው አካል ትብብር ሊጠይቅ ይገባል፡፡

152. ሆኖም በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በኬሚካል ዕቃ ግምጃ ቤትና በተለያዩ መጋዝን ውስጥ የመጠራቀሚያ ጊዜያቸው እየደረሰ እና ያለፈባቸው ያሉ ኬሚካሎች ለመጥቀስ ያህል ብዛት አምስት የሆነ ለብዙ ዓመታት የተቀመጠ ባለ 200 ሊትር የሆነ ናይትሪክ አሲድ እና ሌሎች ኬሚካሎች መኖራቸው ለመጥቀስ ያህል ሶዲየም ሃይድሮጅን ሰልፌት፣ አሴታማይድ፣ ቢስሙዝ፣ ትራይ ፖታሲየም ሳይትሬት እና ሜርኩሪ ኦክሳይድ ሁሉም የአገልግሎቱ ጊዜያቸው እ.ኤ.አ በሐምሌ 2013 ያበቃ መሆኑና ቤንዚን እ.ኤ.አ በ2010 የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ መሆኑ ታውቋል፡፡

153. ጉዳዩን አስመልክቶ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረትና አገልግሎት አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ኬሚካሎቹ ጊዜ ያለፈባቸው እንደሆኑና ለብቻቸው እንደተቀመጡ ያልተወገዱበትም ምክንያት በአገር ውስጥ አቅም የሚፈታ ስላልሆነ እንደሆነ ኬሚካሎቹን ለማስወገድ በፅሁፍ ባይሆንም በስልክ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተነጋገሩ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የተበላሹት ኬሚካሎች ከሌሎች የመጠቀሚ ጊዜያቸው ካላለፈባቸው ኬሚካሎች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ እንደሚገኙ መረጃ በሰበሰብንበት ወቅት ለማየት ችለናል፡፡

154. እንዲሁም የድርጅቱ ሃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት መልስ ለረጅም ጊዜ የቆየው የናይትሪክ አሲድ ኬሚካል አገልግሎት መስጠት መቻሉ በላብራቶሪ ተፈትሾ መረጋገጡና በልዩ ሁኔታ ለማስወገድ ለመንግስት ፋብሪካዎች ጥያቄ እንደቀረበ ገልፀዋል። ሆኖም ከመውጪያ ስብሰባ በኂላ በ30/06/08 ዓ.ም በቁጥር 1/2364/26/02 ለአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሣይንስ ፋክልቲ በርካታ ሌሎች ኬሚካሎች በድርጅቱ እንደሚገኙ ተገልፆ የኬሚካሎቹን አይነት የመለየቱ ስራ እየተሰራ እንደሆነና ሥራው ረጅም ጊዜን እንደሚወስድ፣ ሥራው እንደተጠናቀቀ ዝርዝሮቹን እንደሚያሳውቋቸው ነገር ግን የረጅም ጊዜ ቆይታ ያለው አምስት በርሜል እያንዳንዱ ባላ ሁለት መቶ ሊትር በድምሩ አንድ ሺህ ሊትር የናትሪክ አሲድ ኬሚካል በኬሚካል

ስቶራቸው እንደሚገኝና በርሜሉ ተበልቶ ቢፈነዳ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ ከፍተኛ ስለሚሆን ጊዜ ሳይሰጠው የኬሚካሉ ጥራት እንዲፈተሽላቸው እንደተገለጸ ከተፃፈ ደብዳቤ ለማየት ችለናል፡፡

155. የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ ኬሚካሎች ለአርሦ አደሩ የሚሸጡ መሆናቸው ለምሳሌ አሲቲሊክ 2% ዲፒ ኤክስፓየር ዴት 2013 ብዛት 14,288.65 ኪሎ ግራም የአንዱ ዋጋ በ8.25 ዶላር ጠቅላላ ዋጋ ብር 117,881.36 ዋጋ ያለው እና ከ2 ዓመት በፊት የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ ኬሚካል በድርጅቱ ሱቅ ውስጥ በመሸጥ ላይ መሆኑ እና 2.4 ዲ ኤክስፓይር ዴት 2 ወር ያለፈው ብዛት 3,702 ሊትር የአንዱ ዋጋ 76 ብር ጠቅላላ ዋጋ 281,352 ብር ዋጋ ያለው ከ2 ዓመት በፊት አገልግሎት ጊዜው ያበቃ ኬሚካል በድርጅቱ ሱቅ ውስጥ እየተሸጠ መሆኑ፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፉ ኬሚካሎች በድርጅቱ ሣሪስ ዳማ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ለምሳሌ 2,4D 2,353 ሊትር፣ ዶርስባን 206 ሊትር፣ አክቴሊክ 2% 14,288.45 ኪ.ግ፣ ማላታይን 118 ሊትር፣ ኢንዶሰልፋይን 407 ሊትር፣ ዲያዝኖን 23 ሊትር፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው በመጋቢት 2007 ዓ.ም ያለፈ ኬሚካሎች እስከ 06/01/2008 ዓ.ም ለአርሶ አደሩ ይሸጡ የነበሩ መሆናቸውና በድርጅቱ የሽያጭ መጋዝን ውስጥ ኦዲቱ እስከተከናወነበት ድረስ የነበሩ መሆናቸው ለመጥቀስ ያህልዶርስባን 1,791ሊትር፣ 2,4D 373 ሊትር፣ አክቴሊክ 2% 19.7 ኪ.ግ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

156. የድርጅቱ ሃላፊዎች በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት የተጠቀሱት ጊዜያቸው ያለፉ ኬሚካሎች የመሸጡ ሂደት በአሁኑ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ የቆመ መሆኑንና መሸጡም አግባብ አለመሆኑን እንደታመነበትና እንዲቆም እንደተደረገ ገልፀዋል፡፡

157. በአሰላ ብቅል ፋብሪካ ቀደም ብለው በፋብሪካው ለተለያየ አገልግሎት የተገዙ ኬሚካሎች ያለምንም አገልግሎት በመጋዝንና በላብራቶሪ ክፍል ለረዥም ጊዜ ተከማችተው መቀመጣቸው እና ኬሚካሎችን ለማስወገድ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር እንቅስቃሴ ቢኖርም ኬሚካሎቹ ሊወገዱ አለመቻላቸው፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ልማት ማዕድን አ.ማ በካኦሊን ምርት ፈርጅ እና በቀንጢቻ ክሊኒኮች ውስጥ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ብዛት ያላቸው እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ መድሀኒቶች ተከማችተው እንደሚገኙ በቆጠራ ወቅት መታወቁ ታውቋል፡፡

158. በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት በክሊኒክ ውስጥ የሚገኙ ጊዜ ያለፈባቸው የተወሰኑ መድሀኒቶች እና በንብረት ክፍል የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች አለመወገዳቸው በተጨማሪም የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት ኢ.ማ በናሙና ተወስደው ከታዩ ኬሚካሎች ውስጥ 2 ዓይነት የአበባ ኪሚካሎች እነሱም Teldor 50WG ዋጋው ብር 373,494 impulse 500 El ዋጋው ብር 1,000,792.26 የሆነ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

159. የእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ሃላፊዎች በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት የተተቀሱት ኬሚካሎች ጊዜያቸው ያለፈባቸው መሆናቸውን እና የኬሚካሎቹንም ይዘት በአምራች ድርጅቱ በምርመራ ታውቆ ለሽያጭ የሚውልበትን መንገድ ለማመቻቸት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በቁጥር 01/ነ30/109 ጽፈው በመከታተል ላይ እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

160. ሆኖም ሦስት ኬሚካሎች ማለትም የንግድ ስማቸው ሮቨራል፣ ኦቤሮን እና ስካላ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜያቸው በግንቦት፣ መጋቢት እና ጥር 2012 እ.ኤ.አ እንደቅደም ተከተላቸው መሆኑ እንዲሁም ዴሲስ (19,800 ሊትር)፣ ኢምፐልስ (592 ሊትር)፣ ፍሊንት (237 ኬ.ጂ)፣ ስካላ (206 ሊትር) እና ቴልዶር (160 ኬ.ጂ) የአገልግሎት ማብቂያቸው ሰኔ 2013፣ መስከረም 2013 እና ጥቅምት 2013 እ.ኤ.አ እንደቅደም ተከተላቸው መሆናቸውና ኤክስፓየር ካረጉ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸውን ኬሚካሎች ለሽያጭ ማዋል አደገኛ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

161. በመሆኑም ባየናቸው አብዛኞቹ የልማት ድርጅቶች ያልተወገዱ ኬሚካሎች ስላሉ በመጀመሪያ ደረጃ ድርጅቶቹ ኬሚካሎቹን ሲገዙ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ስለሚያወጡባቸው ከመገዛታቸው በፊት በጥናት በተደገፈ ሁኔታ ሊሸጡ ወይም ቶሎ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን ኬሚካሎች ቢይዙ ድርጅቶቹን ካላስፈላጊ ወጪ ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች በአፋጣኝ ካልተወገዱ ለጤና አደገኛ የሆኑ ስለሆነ በሌሎች ኬሚካሎች ላይ ብልሽት ሊያደርሱ እና በሠራተኞች ጤና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያዎች

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት የንብረት አስተዳደር መመሪያ የተዘጋጀው የካቲት 1996 ዓ.ም መሆኑና ወቅታዊ ሳይደረግ ከአስር ዓመት በላይ መሆኑ፣ በእርሻ መሣሪያዎች እና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማህበር የራሳቸው ንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ የሌለ መሆኑ የሚጠቀሙትም የፌዴራል መንግስት መመሪያን መሆኑ፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት መመሪያው በ2004 ዓ.ም ቢዘጋጅም ነገር ግን በአሰራር ላይ ችግሮች መኖራቸው እንዲሁም ተቆጣጣሪ መ/ቤቱ መንግስት ሙሉ ለሙሉ ባለቤት ለሆነባቸው የልማት ድርጅቶች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ በመጋቢት 2002 ዓ.ም ቢያዘጋጅም እና የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ የካቲት 2006 ዓ.ም ረቂቅ ቢያዘጋጅም አፅድቆ ለልማት ድርጅቶች ያልሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ✓ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ ኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር፣ አዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማዘጋጃ፣ እርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ፣ የፍል ውሀ አገልግሎት ድርጅት እና የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በስራቸው የሚገኙ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ እቃዎች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን በትክክልና በበቂ ሁኔታ እንደማይመዘግቡ ታውቋል፡፡
- ✓ ኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር፣ እርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ፣ የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት እና የግዮን ሆቴሎች ድርጅት በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ የነበራቸውን ንብረት ትክክለኛውን ዋጋ በመነሻ ሂሳብ እንዳልያዙ ታውቋል፡፡
- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ንብረቶች በዕቃ ግምጃ ቤት በስቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡና ከፋይናንስ እስቶክ ካርድ ጋር የማናበብና የማስታረቅ ስራ አለመሰራቱ፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት ቋሚ ዕቃዎች በንብረት መከታተያ መዝገብ ላይ ምዝገባቸው ያለመከናወኑ እንዲሁም በዕቃ ግምጃ ቤት በሰቶክ ካርድ ላይ ያልተመዘገቡና ከፋይናንስ እስቶክ ካርድ ጋር የማናበብና የማስታረቅ ስራ አለመሰራቱ እንዲሁም በእርሻ

መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ ከሐምሌ 2007 ዓ.ም ለተገዙት ቋሚ ዕቃዎች በኮምፒውተር ንብረት መከታተያ መዝገብ ላይ ምዝገባቸው ያለመከናወኑ ተረጋግጧል፡፡

- ✓ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያና ማቅረቢያ ድርጅት እና በእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውነው የሥራ ክፍል የንብረቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ በትክክልና በበቂ ሁኔታ እንደማይዙ ታውቋል፡፡
- ✓ በእርሻ መሳሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ በ2006 በጀት ዓመት በቆጠራ ስራ ላይ የሚመደቡ ሰራተኞች በዓመት ዕረፍት ላይ እያሉ የተመደቡ በመኖራቸው ቆጠራው በወጣለት የጊዜ ገደብ ፀሐፊዎችን አሟልቶ ማስጀመር አለመቻሉ፣ ንብረታቸው የአደራ ቦርድ የሆኑ ንብረቶችን ለረጅም ጊዜ እንቅስቃሴ ሳይኖራቸው በየዓመቱ ቆጠራ የሚከናወን መሆኑ፣ በቁጥር 2 ዕቃ ግ/ቤት ከፍተኛ መጠንና ዋጋ የያዘ የባለአደራ ቦርድ ንብረት እንቅስቃሴው አዝጋሚ የሆነና በየዓመቱ እንቅስቃሴ የሌለው ንብረት መጋዘኑ ለሠራተኞቹ ደህንነት አመቺ አለመሆኑ፣ እንዲሁም በዋናው መሥሪያ ቤት ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 211፣ 212፣ 220፣ 221፣ 223 እና 224 ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ለመቆጠር ቁልፋቸው በማን እጅ እንደሚገኝ ባለመታወቁ መቁጠር አለመቻሉ ታውቋል፡፡
- ✓ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በ2004 በጀት ዓመት የበጀት ዓመት የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ከመዝገቡ ጋር የታረቀበት ምርመራ ለውጭ ኦዲተሮች አለመቅረቡ፣ በ2005 እና 2006 በጀት ዓመት የህትመት መሳሪያዎች መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ካለፉት ጊዜያት ጀምሮ የአመዘጋገብና አያያዝ ችግር የነበረበት እና ያልታረቀ በመሆኑ ከፍተኛ ጉድለት እና ብልጫ ማስከተሉ፣ ከንብረት ምዝገባና ኮስት ትንተና ቡድን ምዝገባ ጋር አለመታረቁ፣ በቆጠራ ወቅት መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው ዕቃዎች መኖራቸው መታወቁ እና በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በ2007 ዓ.ም አላቂ ንብረቶችን በተመለከተ ለመቁጠር ያልተቻለ ሲሆን ይህም በወቅቱ ቢን ካርድ ያልተዘጋጀና ያልቀረበ በመሆኑ ቢን ካርድ መዝጋትና ቆጠራውን ማከናወን አለመቻሉ እና ሠነዶችም ተዘጋጅተው አለመቅረባቸው፣ በዕቃ ግምጃ ቤት ሚገኙ አላቂ የፅህፈትና የንፅህና ንብረቶች በተመለከተ የእቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ በተደራራቢ ሥራ ምክንያትና በህመም ምክንያት ሊገኙ ስላልቻሉ የአላቂ ንብረት ቆጠራ ማከናወን አለመቻሉ፣ በየቢሮው ውስጥ ያሉት ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር (ታግ) ያልተለጠፈባቸው

ስለሆነ ንብረቶችን ለመለየት ማስቸገሩ በተጨማሪም የንብረት ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የቆጠራ ቡድኑ፣ አስቆጣሪው አካል ቢኖሩም ታዛቢ ግን አለመኖሩ ታውቋል፡፡

- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች ውስጥ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በመጋዘን ሃላፊና ረዳት ሃላፊ ከተመደቡት 17 ሠራተኞች ውስጥ 8ቱ በንብረትና ተዛማጅነት ባለው የትምህርት መስክ ያልሰለጠኑ መሆናቸው እንዲሁም በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት በግዥ ንብረት አስተዳደር እና በትራንስፖርት ዳይሬክቶሬት ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች ላይ በመጋዘን ሃላፊ ከተመደቡት 30 ሠራተኞች ውስጥ 8ቱ በንብረትና ተዛማጅነት ባለው የትምህርት መስክ ያልሰለጠኑ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡
- ✓ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት ተሽከርካሪዎች በሰሌዳ ቁጥር የሚመዘገቡበት ሬጅስተር ተሟልቶ አለመያዝ እና ተሽከርካሪዎች ሊብሬ በሥርዓት በአንድ ቦታ ተሟልቶ አለመያዝ፣ በግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የድርጅቱ ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ያሉ መረጃዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ እና በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት ድርጅት ለተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ምዝገባ የሚያከናወነው በፋይናንስ ንብረትና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ስር በሚገኘው የድርጅቱ ንብረት የሆኑ ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ያሉ መረጃዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ ታይቷል፡፡

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣

- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ፣ በግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ.ማ እና በኮስቲክ ሶዳ አክስዮን ማህበር ቋሚም ንብረቶች ለአደጋ በተጋለጠ ሁኔታ የሚገኙ መሆናቸው ታውቋል፡፡
- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች ማካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅራቢ ኢንሹራንስ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና እንደማይገቡላቸውና የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ እንደማያዘጋጁላቸው ታይቷል፡፡

- ✓ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በግብርና ምርት ማሳደጊዎች አቅራቢ ድርጅት፣ በእርሻ መሣሪያዎችና ቴክኒክ አገልግሎት አ/ማ እና በአትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አ.ማ ለአንዳንድ ቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር እንደማይሰጣቸውና የመለያ ቁጥሩ በቋሚ ንብረቱ ላይ እንደማይፃፍ ወይም እንደማይለጠፍ እንዲሁም ሊለቅ በሚችል ማርከር ለንብረቶች መለያ ቁጥር እንደሚሰጥ ተረጋግጧል፡፡
- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎችና ማቅረቢያ ድርጅት እና በህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት ንብረታቸውን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከልና ተስማሚ የንብረት መጋዘን እንደሌላቸው ታውቋል፡፡

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣

- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎችና ማቅረቢያ ድርጅት፣ አሰላ ብቅል ፋብሪካ፣ የህንፃ ዕቃዎች አቅራቢ ድርጅት፣ የፍል ውሀ አገልግሎት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ልማት ማዕድን አ.ማ፣ የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማ እና አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት በርካታ ለብዙ ዓመታት ጥቅም ሳይሰጡ ቆመው ያሉ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣ የተለያዩ መሣሪያዎችና ዕቃዎች፣ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ማሽኖችና የቢሮ መገልገያና ቁሳቁሶች አሮጌ ንብረቶች እና አዳዲስ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ሳይወገዱ ያሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡
- ✓ በናሙና ካየናቸው የልማት ድርጅቶች መካከል የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በግብርና ምርት ማሳደጊያዎችና ማቅረቢያ ድርጅት፣ በአሰላ ብቅል ፋብሪካ፣ በኢትዮጵያ ልማት ማዕድን አ.ማ፣ በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት እና በእርሻ መሣሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አ.ማ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች መኖራቸውና ያልተወገዱ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

ሀ/የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

- ✓ በናሙና ካየናቸው ድርጅቶች ለማየት እንደተቻለው በአንዳንዶቹ የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ አለመኖሩና በአንዳንዶች ደግሞ ቢኖርም የተሟላ አለመሆኑ በዚህም ምክንያት ወጥ የሆነ መመሪያ ከመፍጠር አንፃርና ለቁጥጥርና ክትትልም አመቺ እንዲሆን ኤጀንሲው በአፈፃፀማቸው አስተማሪ ከሆኑ የልማት ድርጅቶች ቤንችማርክ በመወሰድ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልና ችግራቸውን ሊቀርፍ የሚያስችል የንብረት አስተዳደርና አወጋገድ መመሪያ አዘጋጅቶ ለድርጅቶቹ ማሰራጨት ይኖርበታል፡፡
- ✓ ካየናቸው የልማት ድርጅቶች ለመረዳት እንደተቻለው በልማት ድርጅቶቹ ባለሙያዎች ዘንድ የእውቀትና ክህሎት ክፍተት በመኖሩ ክፍተታቸውን ለመሙላትና የመንግስት ሃብት የሆኑትን ንብረቶች በተሟላ ሁኔታ ለመመዝገብና እንዲጠበቁ ለማድረግ ፈፃሚ አካላቱን በሚቻል መልኩ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ክህሎታቸው እንዲሻሻል ኤጀንሲው ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ የነበራቸውን ንብረት ትክክለኛው ዋጋ ትክክለኛ በሆነ መንገድ ካልተመዘገበ ለብልሹ አሰራር መንገድ ስለሚከፍት ኤጀንሲው በተለይ ድርጅቶች ሲዋሃዱ፣ ለሌሎች ድርጅቶች ንብረት ሲያከፋፍሉ ወይም ንብረት ከሌሎች ሲያገኙ በትክክል ስለመመዝገባቸው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ✓ ኤጀንሲው በአፈፃፀማቸው ላቅ ካሉ ድርጅቶች ቋሚ ንብረቶችን በኮምፒውተር ምዝገባ ሲያከናውኑ የሚጠቀሙትን አሰራርና ፎርማት በመውሰድ ስልጠና በመስጠት የቋሚ መዝገባቸውን በተጠናቀረ ሁኔታ እንዲይዙ ማገዝ ይኖርበታል፡፡
- ✓ በልማት ድርጅቶቹ የንብረት አስተዳደር የሚያከናውኑት የሥራ ክፍሎች የተጠናቀረ መረጃ የያዘ የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ እንዲያዝ ከተፈለገ የሰው ሃይላቸው በክህሎት የላቀ መሆን ስለሚኖርበት በተለይ ላቅ ያሉ አፈፃፃም ካሳዩ ድርጅቶች

ልምዳቸው በመውሰድ ኤጀንሲው ለባለሙያዎቹ ክፍተታቸውን እንዲያሟሉ ስልጠና ሊሰጥ ወይም ሁኔታዎችን ሊያመቻች ይገባል፡፡

- ✓ ቆጠራ የሚከናወነው የመንግስት ንብረቶች በትክክል መኖራቸውንና መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ ቢሆንም በአንዳንድ የልማት ድርጅቶች ቆጠራው በትክክል አለመካሄዱ ንብረቶቹን ለብክነት ስለሚዳርግ በመሆኑም ኤጀንሲው ቆጠራው በየዓመቱ ስለመከናወኑና በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የተከናወነ ስለመሆኑ ቁጥጥር ሊያካሂድ፣ በቆጠራው ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች የስራ አመራሩና ቦርዱ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ አቅጣጫ ሊሰጥ እንዲሁም የውጭ ኦዲተሮች በታዛቢነት ስለመኖራቸው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ✓ መንግስት ከፍተኛ ገንዘብ ከሚያወጣባቸው ንብረቶች አንዱና ዋነኛው ተሽከርካሪ ቢሆንም ነገር ግን ባየናቸው ድርጅቶች በርካታ ሊባሉ የሚችሉ የራሳቸውም ሆነ የሌሎች ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት የተቀመጡ ቢሆንም አሁንም የበለጠ ከመበላሸታቸው በፊት ኤጀንሲው ከድርጅቶቹ የሥራ አመራርና የቦርድ አካላት ጋር በመሆን የመንግስትን ንብረት ከብክነት ለማዳን አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ግፊት ሊያደርግ ይገባል፡፡

ለ/ ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን በተመለከተ፣

- ✓ የመንግስት ንብረቶች ለተወሰነላቸው ዓላማና ተግባር ብቻ እንዲውሉ ከተፈለገ የልማት ድርጅቶቹ የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር ይገባል ይሄን ለማድረግ አይነተኛ ሚና የሚጫወቱት የድርጅቶቹ የውስጥ ኦዲተሮች ስለሆኑ ኤጀንሲው ለነሱ የሚሰጠውን ድጋፍ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል በተጨማሪም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በየጊዜው ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታውን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ኢንሹራንስ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና ሊገቡላቸውና የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ ሊያዘጋጁላቸው ይገባል፡፡
- ✓ በመንግስት ልማት ድርጅት የሚገኝ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት ከጥፋትና ከስርቆት ለመጠበቅ የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ሊሰጠውና የመለያ ቁጥሩ በቋሚ ንብረቱ ላይ ሊፃፍ ወይም ሊለጥፍ ይገባል፡፡
- ✓ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረታቸውን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከል ተስማሚ የንብረት መጋዘን ሊኖራቸውና በተለይ ባየናቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች በመጋዘን

ውስጥ ሊቀመጡ የማይችሉ በርካታ ንብረቶች መኖራቸው እነዚህ ንብረቶች ለፀሃይና ለዝናብ በማይጋለጡበት መልክ ቦታ ተለይተው ሊቀመጡና ከስርቆትና ከብክነት ሊጠበቁ ይገባል፡፡

ሐ/ የንብረት አወጋገድን መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣

- ✓ በርካታ ለብዙ ዓመታት ጥቅም ሳይሰጡ ቆመው ያሉ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣ የተለያዩ መሣሪያዎችና ዕቃዎች፣ አልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ማሽኖችና የቢሮ መገልገያና ቁሳቁሶች አሮጌ ንብረቶች እና አዳዲስ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች ሳይወገዱ በልማት ድርጅቶቹ ይገኛሉ በመሆኑም ኤጀንሲው የበለጠ ንብረቶቹ አደጋ ሳይደርስባቸው ድርጅቶቹ ንብረቶቹን እንዲያስወገዱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ትብብር በማድረግ በአፋጣኝ እንዲወገዱ አስፈላጊውን እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች እና መድሀኒቶች በናሙና ባየናቸው የልማት ድርጅቶቹ ስለሚገኙ ኤጀንሲው አስፈላጊውን እገዛ ከሚመለከተው አካል ትብብር በመጠየቅ በሰራተኞቹ ላይ አደጋ ሳይደርስ በአፋጣኝ እንዲወገዱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገልን ከፍተኛ የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት አካባቢ፡ *የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደር ኢኮኖሚያዊ፣ ስኬታማና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣*

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issues)	የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)	ምርመራ
የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደርን ለማከናወን የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲሁም ውጤታማ፣ ኢኮኖሚን ማዕከልና ስኬታማ በሆነ መልኩ ንብረቶቹ መጠበቃቸውን መገምገም፣	**የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**	
	1. የመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚመለከተው የበላይ አካል የጸደቀ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ሊኖራቸውና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡	
	2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በስራቸው የሚገኙ ቋሚ ንብረቶችና አላቂ እቃዎች ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎችን በዓይነት፣ በመጠንና በብዛት በመለየት መረጃቸውን በአግባቡና በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ሊይዙ ይገባል፡፡	
	3. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዲስ መልክ ሲቋቋሙ የነበራቸውን	

	ንብረት ትክክለኛው ዋጋ በመነሻ ሂሳብ ሊይዙ ይገባል፡፡	
	4. የንብረት አስተዳደር የሚያከናውነው የሥራ ክፍል የተጠናቀረ መረጃ የያዘ የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ መያዙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም መዝገቦች ወቅታዊ መደረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡	
	5. የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውነው የሥራ ክፍል የንብረቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ ሊይዙ ይገባል፡፡	
	6. የመንግስት የልማት ድርጅቶች በየዓመቱ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ሊያካሂዱና የቆጠራ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በቆጠራው የተገኘውም ከምዝገባው ጋር ማመዛዘን ይኖርባቸዋል፡፡	
	7. ለንብረት ስራ የሚመደቡ ሰራተኞች ቢቻል በሙያው ወይም ተዛማጅነት ባለው የትምህርት ዘርፍ የሰለጠኑ መሆናቸው	

	ሊረጋገጥ ይገባል፡፡	
	8. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ያከናወኗቸውን የግንባታ ሥራዎች እንደ ቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ መመዝገብ አለባቸው፡፡	
	9. የልማት ድርጅቶች በእርዳታ ወይም በስጦታ የሚያገኙዋቸውን ንብረቶች ዋጋ እና የአገልግሎት ዘመናቸውን የሚገልጽ መረጃ ከለጋሾች ወይንም ከሰጡት አካላት መጠየቅ እና ከድርጅቱ የቋሚ ንብረቶች በተለየ የንብረት መመዝገቢያ ካርድ ላይ መመዝገብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም መረጃው ካልተገኘ በግምት ዋጋው መመዝገብ ይኖርበታል፡፡	
	10. የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ከተገዙ ጊዜ ጀምሮ ያሉ መረጃዎች ለተሽከርካሪውና ለመሳሪያው የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መዝግበው ሊይዝ ይገባል፡፡	
	ንብረቶቹ በትክክል መጠበቃቸውንና ለተገቢ ዓላማ መዋላቸውን	

	በተመለከተ፣	
	1. ቋሚም ሆነ አላቂ እቃ ለተወሰነላቸው ዓላማና ተግባር ብቻ ሊውሉ ይገባል፡፡ እንዲሁም ንብረቶቹ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጡ ተገቢ የጥገና እና የእንክብካቤ ሥርዓት ሊዘረጋላቸው ይገባል፡፡	
	2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ኢንሹራንስ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ንብረቶች የመድን ዋስትና ሊገቡላቸውና የኢንሹራንስ መከታተያ መዝገብ ሊያዘጋጁላቸው ይገባል፡፡	
	3. በመንግስት ልማት ድርጅት የሚገኝ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ሊሰጠውና የመለያ ቁጥሩ በቋሚ ንብረቱ ላይ ሊፃፍ ወይም ሊለጥፍ ይገባል፡፡	
	4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረታቸውን ከአደጋና ከብልሽት የሚከላከልና ተስማሚ የንብረት መጋዘን ሊኖራቸው ይገባል፡፡	
	5. የቋሚ ንብረቶቹ ያሉበት አቋም ወይም የሚገኙበት	

	ቦታ ላይ ለውጥ ቢኖር ይኸው በቋሚ ንብረት ካርዱ፣ በቋሚ ንብረት መዝገብ እና በጠባቂዎች ንብረት ወይም የመጋዘን ሃላፊ ዝርዝር ውስጥ እንዲመለከት ሊደረግ ይገባል፡፡	
	6. ዋጋቸው ከብር 1000 በታች ሆነው ያገልግሎት ዘመናቸው ከአንድ ዓመት በላይ የሆኑ ንብረቶች ለብክንት ሊዳረጉ ስለሚችሉ ለብቻ መዝግቦ በመያዝ የወጪና የገቢ እንቅስቃሴያቸውን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡	
የመንግስት የልማት ድርጅቶች የንብረት አወጋገድን ለማቀላጠፍ የሚያስችል የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑንና ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ንብረቶች አወጋገድ ስኬታማና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፣	***የንብረት አወጋገድ መረጃ አያያዝ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን በተመለከተ፣***	
	1. የመንግስት ልማት ድርጅቶች በሚመለከተው የበላይ አካል የጸደቀ የንብረት አወጋገድ መመሪያ ሊኖራቸውና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡	
	2. የልማት ድርጅቶች በስራቸው የሚገኙ ንብረቶች ሲያስወግድ የተወገዱትን ንብረቶች ዝርዝር መረጃ የሚይዝበት አሰራር	

	ሊዘረጋ ይገባል፡፡	
	4. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ያስወገዱትን ንብረት የእርጅና ተቀናናሹን ወዲያውኑ ከንብረት መዝገብ ሊሰርዙና ቋሚ ንብረቱን በማስወገድ የተገኘ ትርፍም ሆነ ኪሳራ ንብረቱ በተወገደበት የሂሳብ ዘመን ሊመዘግብ ይገባል፡፡ እንዲሁም ከሽያጭ (ተሸከርካሪዎችና መሣሪያዎች ከሆኑ) የተገኘውም ገቢ ወዲያውኑ ለመንግስት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡	
	ንብረት አወጋገድን በተመለከተ፣	
	1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ንብረት ከማስወገዳቸው በፊት ሊገለገሉበት ያለመቻላቸው በኮሚቴ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡	
	2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለሚያስወግዱዋቸው ንብረቶች የሚያስወግዱበት ዘዴ እና ወቅታዊ የገበያ ዋጋቸውን በቅድሚያ በኮሚቴ ሊጣራ ይገባል፡፡	
	3. የመንግስት የልማት	

	ድርጅቶች ለሚወገዱ ንብረቶች የሚወጡ ጨረታዎችን ጥሪ የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ተሳታፊዎችን ሊደረስ የሚችል መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡	
	4. የሚወገዱ ንብረቶችን በጨረታ ለመግዛት የተጫረቱ ባለሃብቶችን አሸናፊ ተሸናፊ ከለየ በኋላ ውጤቱን የሚሳውቅበት መንገድ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት ሊሆን ይገባል፡፡	
	5. ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለሚወገዱ ንብረቶች ተመሳሳይ ንብረቶች የሚወገደው የንብረት አወጋገድ ስርዓት ወጥና ግልፅ አሰራርን የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡	
	6. እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸው ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ባሉበት ሁኔታ በመሸጥ ወይም መለዋወጫቸውን ፈትቶ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በውዳቂ ብረታ ብረትነት እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡	
	7. የመንግስት የልማት	

	ድርጅቶች ንብረት ያስወገዱት በሽያጭ መልክ ከሆነ የሽያጭ ዋጋው በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቀበልና ገንዘቡም በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡	
	8. የልማት ድርጅቶች የሚወገዱ ንብረቶች በባህሪያቸው ለጤና አደገኛ የሆኑ ኬሚካሎች ወይም መድሀኒቶች ወይም የጨረር ጉዳት የሚያስከትሉ ሆነው ሲገኙ በአወጋገድ ላይ አስፈላጊውን እገዛ ከሚመለከተው አካል ትብብር ሊጠይቅ ይገባል፡፡	
	9. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቋሚ ንብረት ሲሸጥ፣ ለሌላ ሲተላለፍ ወይም ሲወገድ የመድን ሽፋን ውሉን በወቅቱ እንዲቋረጥ ሊያደርጉ ይገባል፡፡	
ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶችን ለመምራት	**ኤጀንሲው ለድርጅቶቹ አስፈላጊውን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፣**	
	1. ኤጀንሲው በመንግስት ልማት ድርጅቶቹ	

የሚያስችል መመሪያዎችን ማውጣቱንና ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ማድረጉ እንዲሁም ከልማት ድርጅቶቹ ጋር በቅንጅት የሚሰሩት ሥራዎች ስኬታማና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀሙን መገምገም፣	የሚገኙ የሚወገዱ ንብረቶችን አያያዝና አወጋገድ በሚመለከት በመረጃ ቋት በመያዝ በየዓመቱ የየትኛው መ/ቤት፣ ምን ያህል እና የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዕቅዱ መሠረት እየተፈፀመ መሆኑን በመገምገም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡	
	2. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶች የሚመሩባቸውን የተለያዩ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎችን ሊያዘጋጅና አፈፃፀማቸውን ሊከታተል በተጨማሪም ለልማት ድርጅቶቹ አፅድቆ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡	
	3. ኤጀንሲው በልማት ድርጅቶች መካከል ቅንጅትና ትስስር እንዲኖር ሊደርግ ይገባል፡፡	
	ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፣	
	1. ኤጀንሲው ንብረት ከሚወገድላቸው የልማት ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ	

	እና አወጋገድ ዙሪያ ውይይት የሚደረግበት መደበኛ እና ተከታታይ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ሊያዘጋጅና በውይይቱ ለሚነሱ ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡	
	2. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚወገድ ንብረቶችን ለሌላ አካል በስጦታ ሲያስተላልፉ በስጦታ የተላለፈለት ድርጅት ሕጋዊ መሆኑ ሊረጋገጥና ርክክብ የተፈጸመበትን ሰነድ አገልግሎቱ በግልባጭ እንዲያውቀው ሊያደርግ ይገባል፡፡	
	3. ኤጀንሲው የልማት ድርጅቶቹን ከድርጅቶቹ ጋር በቅንጅት በመሆን ንብረት ማስወገድ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያስወገዳቸውን እና ገና የሚወገዱ ተሽከርካሪዎችና ንብረቶችን ዝርዝር መረጃ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡	